ዲላ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስ ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በ2007 የተዘጋጁ የሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ይዘት አመራረጥ እና አደረጃጀት ፍተሻ

በ

ካሳሁን ኩራባቸው

ዲላ ዩኒቨርስቲ

ጥር 2011 ዓ.ም

# ዲላ ዩኒቨርሲቲ


የማህበራዊ ሳይንስ ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ- ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር


# በ2007 የተዘጋጁ የሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ይዘት አመራረጥ እና አደረጃጀት ፍተሻ

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር መስክ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት


በ

ካሳሁን ኩራባቸው

የጥናቱ አማካሪ

ኢዮብ ቀለመወርቅ (ዶ/ር)        ዲላ ዩኒቨርሲቲ

ጥር 2011 ዓ.ም

# ዲላ ዩኒቨርሲቲ

## የማህበራዊ ሳይንስ ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ- ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በ2007 የተዘጋጁ የሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ

መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ይዘት አመራረጥ እና

አደረጃጀት ፍተሻ

አማርኛ ቋንቋ በማስተማር መስክ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት

በ

ካሳሁን ኩራባቸው

ጥር 2011 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም______________________________________ ፊርማና ቀን______________________

የውጭ ፈታኝ _________________________________ ፊርማና ቀን______________________

የውስጥ ፈታኝ_________________________________ ፊርማና ቀን______________________

## ማረጋገጫ

‹‹በ2007 የተዘጋጁ የሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ይዘት አመራረጥ እና አደረጃጀት ፍተሻ›› በሚል ርዕስ በዲላ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና የሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር አማርኛ ቋንቋን በማስተማር መስክ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ ወጥ የራሴ መሆኑን፣ የተጠቀምኩባቸውም ድርሳናት በትክክል ዋቢ መሆናቸውንና ዲላ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ካሳሁን ኩራባቸው

ጥር 2011 ዓ.ም

# ምስጋና

በመጀመሪያ ስንቱን ውጣ ውረድ አልፌ እዚህ ለመድረስ ያበቃኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። በመቀጠልም ይህ ጥናት ከግብ እንዲደርስ ከጅምር እስከ ፍጻሜ ድረስ ባለመሰልቸት በማረም እና አቅጣጫ በማስያዝ ላደረጉልኝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አማካሪዬን ዶ/ር ኢዮብ ቀለመወርቅ ከልብ አመሰግናለሁ። ትምህርቴን ያለ ሀሳብ በአግባቡ  እከታተል እችል ዘንድ ልጆቼን ለተንከባከብሽልኝ ውድ ባለቤቴ መምህርት ዘሪቱ ከበደን እጅግ በጣም አድርጌ ላመሰግንሽ እወዳለሁ።

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ ii
የሠንጠረዥ ማውጫ ........ v
አጠቃሎ ........ vi
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 2
1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ ........ 2
1.3.2. የጥናቱ ንዑስ ዓላማ ........ 2
1.4. የጥናቱ ጥያቄዎች ........ 3
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3
1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 3
ምዕራፍ ሁለት ........ 4
ክለሳ ድርሳን ........ 4
2.1. የሰዋስው ምንነት ........ 4
2.2. የሰዋስው ይዘቶች አመራረጥ ........ 7
2.2.1. ትክክለኛነት ........ 8
2.2.2. ግልፅነት ........ 8
2.2.3. ተመጣጣኝነት ........ 9
2.2.4. ተገቢነት ........ 9
2.3. የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀት ........ 9
2.3.1. ተከታታይነት ........ 10

2.3.1.1. የሰዋስው ትምህርቶች ይዘትና አቀራረብ ..... 10

2.3.1.1.1. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ..... 10

2.3.1.1.2. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ..... 11

2.3.2. ተለጣጣቂነት ..... 11

2.4. የተዛማጅ ጥናቶች ቅ✂ት ..... 12

ምዕራፍ ሦስት ..... 16

3.1. የጥናቱ ዘዴ ..... 16

3.2. የመረጃ ምንጮች ..... 16

3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ..... 17

3.4. የመማሪያ መጽሐፍ የክፍል ደረጃ አመራረጥ ..... 17

3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ ..... 17

ምዕራፍ አራት ..... 19

የመረጃ ትንተና ..... 19

4.1. ስለ መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ መረጃ ..... 19

4.1.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ..... 19

4.1.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ..... 20

4.2. በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ አንፃር ..... 21

4.2.1. የመማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ ይዘት ከግልጽነት አንፃር ..... 21

4.2.1.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ..... 22

4.2.1.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ..... 24

4.2.2. የመማሪያ መጽሐፍ ብቃት ከትክክለኛነት አንፃር ..... 27

4.2.2.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ..... 28

4.2.2.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ..... 30

4.2.3. የመማሪያ መጽሐፍ ከተመጣጣኝነት አንፃር ..... 32

4.2.3.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ..... 33

4.2.3.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ..... 34

4.2.4. የመማሪያ መጽሐፍ ከተገቢነት አንጻር ..... 34

4.2.4.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ............ 35

4.2.4.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ............ 35

4.3. የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀት ............ 35

4.3.1. ከተከታታይነት አንጻር ............ 35

4.3.1.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ............ 36

4.3.1.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ............ 39

4.3.2. የመማሪያ መጽሐፍ ከተለጣጣቂነት አንፃር ............ 41

4.4. የመማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው አቀራረብ ገፅታ ............ 43

4.4.1. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ............ 43

4.4.1.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ............ 43

4.4.1.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ............ 45

4.4.2. የመማሪያ መጽሐፍ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ ገጽታ ............ 47

4.4.2.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ............ 47

4.4.2.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ............ 50

4.4.3. የመማሪያ ሁለቱን የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ በስብጥር የመጠቀም ገጽታ ............ 51

4.4.3.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ............ 52

4.4.3.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ............ 52

ምዕራፍ አምስት ............ 54

ማጠቃለያ እና አስተያየት ............ 54

5.1.ማጠቃለያ ............ 54

5.2. አስተያየት ............ 55

ዋቢ ፅሁፎች ............ 56

## የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ ገጽ

ሠንጠረዥ1. የታላሚ መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ መረጃ ...............................20

ሠንጠረዥ2. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይዘት...........................20

ሠንጠረዥ3. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይዘት-...........................21

ሠንጠረዥ4. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የግልፅነት ችግር.............23

ሠንጠረዥ5. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በታላሚው ቋንቋ አቻ ፍቺ እያላቸው የተውሶ ቃላት...................................................27

ሠንጠረዥ6. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቃላት እና የሀረግ ስያሜ ትክክለኛነት ችግር እንዲሁም የሰዋስው ገለፃ ትክክለኛነት ችግር....29

ሠንጠረዥ7. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተመጣጣኝነት ገፅታ.........................................34

ሠንጠረዥ8. የ8ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ውሰጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተመጣጣኝነት ገፅታ..................................................................35

ሠንጠረዥ9. የ7ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን ...................................................................37

ሠንጠረዥ10. የ8ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን....................................................................40

ሠንጠረዥ11. የ7ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ሁለቱን የሰዋስው ይዘቶች በስብጥር

የመጠቀም ገፅታ..........................................................................53

ሠንጠረዥ12. የ8ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ሁለቱን የሰዋስው ይዘቶች በስብጥር

የመጠቀም ገፅታ ..........................................................................53

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የተስማማ አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል ላይ የተካሔደ ጥናት ነው።

የጥናቱ ዋነኛ ትኩረት በ2007 የተዘጋጁ የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ይዘት አመራረጥ እና አደረጃጀት መገምገም የጥናቱ አብይ ስራ ነው።

ይህን የጥናቱን አብይ ትኩረት መነሻ በማድረግ በታላሚዎቹ የክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙት መጽሐፍ በጥልቀት በመፈተሸ የታላሚዎቹን መጽሐፍ የሰዋስው ይዘቶች አመራረጣቸውን እና አደረጃጀታቸውን በምን መልኩ እንደተደራጁ እንዲሁም የመጽሐፉን ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸውን መፈተሸ የዚህ ጥናት ዋነኛው መዳረሻ ነው።

በዚህም መሰረት በየመማሪያው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበ የሰዋስው ይዘቶችም ከአመራረጥ ከትክክለኛነት፣ ከግልጽነት፣ ከተመጣጣኝነት እና ከተገቢነት አንፃር አደረጃጀትን በተመለከተ ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነትን እንዲሁም አወቃቀርን በተመለከተ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና የሁለቱንም ስብጥራዊ አጠቃቀም ገጽታ ለማየት ተሞክሯል።

በዚህ ጥናት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ እና አደረጃጀት በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት ፅንስ ሃሳባዊ መርሆች አንፃር በማየት ተተንትነዋል።

በዚህ መሰረት በታላሚ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች ላይ መጠነኛ የአመራረጥ እና የአደረጃጀት ችግሮች መታየታቸውን በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል።

በመጨረሻም በዚህ ጥናት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አመራረጥ እና አደረጃጀት ላይ የታዩ ድክመቶችን ለማረም ያስችላሉ የተባሉ አስተያየቶችን በአጥኚው እንደ መፍትሔ ሃሳብነት ለማቅረብ ተሞክሯል። ይኸውም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ የታዩትን የአመራረጥ እና የአደረጃጀት ችግሮችን ለማስወገድ ትኩረት መስጠት በመማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ወቅት ተማሪዎች፣ መምህራን እና የትምህርት ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡ እድሉን ማመቻቸት፣ ምጋቤ መልሶችንም ተግባራዊ ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የመማሪያ መጽሐፍ የታቀደውን አላማ ከዳር ለማድረስ እንዲያስችሉ ያላቸውን አቅም ለመረዳት በተለያዩ ጊዜያት መገምገም አለባቸው፡፡ የመማሪያ መጽሐፍን መገምገም አስፈላጊነት Sheldon(1988) ሲገልፁ የመማሪያ መጽሀፍን በሁለት ምክንያቶች ልንገመግማቸው እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡

የመጀመሪያው ደረጃ ለመምህራን የተሻሉትን የመማሪያ መጽሐፍ ለመምረጥ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በመማሪያ መጽሐፍ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ሊኖር እንደሚችሉ መምህራን እንዲያወቁ ያግዛል ሲሉ ያስገነዝባሉ፡፡

የመማሪያ መጽሐፍ የመገምገሚያ ደረጃዎች ሶስት ናቸው፡፡ እነርሱም ቅድመ አገልግሎት፣ በአገልግሎት ጊዜና ድህረ አገልግሎት ናቸው (Cunnings Worth,1995) እና (Elis,1997)፡፡ ከአገልግሎት በፊት የሚደረግ የመጽሐፍ ግምገማ መምህሩ ለማስተማር ተግባሩ የተሻለውን እና ትክክለኛውን መጽሐፍ እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡ በአገልግሎት ጊዜ የሚደረግ የመጽሐፍ ግምገማ መምህራን የመጽሐፉን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ለማወቅ ይረዳቸዋል፡፡ ከአገልግሎት በኋላ የሚደረግ ግምገማ ደግሞ ከተወሰነ የመማር ማስተማር ሂደት በኋላ መምህራን የመጽሐፉን ጥራት እና ብቃት ለመግለፅ ያስችላቸዋል፡፡

የመማሪያ መጽሐፍ ግምገማ መምህሩ በነፃነት እና በራስ በመተማመን የሚያስተምረውን ትምህርት እንዲቆጣጠረው ያስችለዋል፡፡ አልፎ ተርፎም እራሱን መምህሩን መልሶ በማሰልጠን ምን?፡ መቼ?፡ እንዴት?፡ ለማን?፡ እንደሚያስተምር እና እንደሚፈትን ግንዛቤ ይሰጣል (Nunan and Lamb,1996:185)፡፡ በጥቅሉ የመማሪያ መጽሐፍ የሚገመገሙበት አቢይ ምክንያትም የመማሪያ መጽሐፍ ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት የተሻሉ የማስተማሪያ መጽሐፍ ለመምህራን እና ተማሪዎች ለማቅረብ ነው፡፡

በመማሪያ መጽሐፍ ግምገማ ትኩረት ከሚደረግባቸው ጉዳዮች መካከል በትምህርትነት የቀረቡ ይዘቶች ግምገማ ዋና ተጠቃሽ ነው። በሀገራችን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የቋንቋ ክሂልን፣ የሰዋስውን እና የስነ-ጽሁፍ ችሎታን ለማጎልበት የተመረጡ ናቸው (Nunan and Lamb, 1996:185)። በመሆኑም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ግምገማ አንዱ ተተኳሪ ጉዳይ ነው።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የእነዚህ ተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍ የክፍል ደረጃዎች የተመረጡበት ዋነኛ ምክንያት ተማሪዎች የታላሚዎቹን የክፍል ደረጃ ካጠናቀቁ በኋላ ወደ አገር አቀፍ የትምህርት እርከን የሚሸጋገሩበት ደረጃ በመሆኑ የክልሉ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ዝቅተኛ መሆን አጥኚው ይህን የክፍል ደረጃ እንዲመርጥ አስችሎታል።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት በ2007 ዓ.ም. በአገልግሎት ላይ የሚገኙ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት አመራረጥ እና አደረጃጀትን መገምገም ነው።

### 1.3.2. የጥናቱ ንዑስ ዓላማ

የጥናቱ ዝርዝር አላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡-

- በተተኳሪ የመማሪያ መጽሐፍ ከሰዋስው ትምህርት አመራረጥ እና አደረጃጀት አኳያ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች መመርመር፤
- ጥናቱ በጠንካራ ጎንነት የሚያቀርበውን ሰዋስዋዊ ትምህርትን በግብዓትነት መጠቀም መቻሉን መፈተሽ፤
- በመማርያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የቋንቋ ማስተማር አላማዎች አደረጃጀት ተገቢነት መፈተሽ ነው፤
- የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ይዘታቸው ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው።

## 1.4. የጥናቱ ጥያቄዎች

- ❖ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ እና አደረጃጀት ምን ይመስላል?
- ❖ በመማሪያ መጽሐፍ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምን ይመስላሉ?
- ❖ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ለታዩ ደካማ ጎኖች የመፍትሄ ሀሳቦች ምንድ ናቸው?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል፡፡

- ✓ በተተኳሪ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘትና አደረጃጀትን በመፈተሽ በቀጣይ የመማሪያ መጽሐፍ ለሚያዘጋጁ አካላት ግብአት ይሆናል፡፡
- ✓ በተተኳሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ እና አደረጃጀት ምን ገፅታ እንደነበረው በመለየት ለሌሎች ክልሎች ማሳያ ይሆናል፡፡
- ✓ በተተኳሪ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ እና አደረጃጀት ያሳዩትን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይቶ በማመልከት ደካማ ጎናቸው ፀድተው ጠንካራዎች እንዲበረታቱ ለቀጣይ አዘጋጆች ፍንጭ ይሰጣል፤ ለታላሚው ቋንቋም መገልበት አይነተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በ2007 ዓ.ም. ጀምሮ ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው ሳይክል ተማሪዎች ተዘጋጅተው በስራ ላይ ያሉ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ እና አደረጃጀት ተተኳሪ በማድረግ ጎን ለጎን በማነፃፀር ማየት ነው፡፡

በሌላ መልኩ ይህ ጥናት ከሰዋስው ይዘት መርሆች ውስጥ ተገቢነትን በተመለከተ የመርሃ ትምህርቱንና የመማሪያ መጽሐፍ ከሰዋስው ይዘት አኳያ መጣጣማቸውን ብቻ ይመለከታል፡፡ እንዲሁም ከአደረጃጀት አኳያ ተለጣጣቂነትን በተመለከተ በማየት መገምገም ነው፡፡

ይህ ጥናት በርእሱ በተጠቀሰው ዘመን ውስጥ ከክልሉ ትምህርት ቢሮ ሀላፊነት ውጭ ወይንም ለሌሎች ክልሎች የሚዘጋጁትን አይመለከትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

## 2.1. የሰዋስው ምንነት

ሰዋስው የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ ቀደምት የቋንቋ ምሁራን እንደ አተያያቸው አድማስ የተለያየ ብያኔ ሰጥተውታል፡፡ ሰዋስው ማለት መሰላል፣ ዕርከን ከታች ወደ ላይ፣ከላይ ወደታች መመላለሻ ፣ደረጃ መውጫና መውረጃ ማለት ነው (ደስታ፡1992፡9)፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የአማርኛ መዝገበ ቃል (1993፡121)‹‹ሰዋስው ማለት የቃላት አመሰራረት የአረፍተ ነገር አሰካክ ስርዓት ወይም ህግ ነው›› ይሉታል፡፡

Crystal, (2004:6) በበኩላቸው📖ሰዋስው ቋንቋ እንዴት ሊተገበር እንደሚችል ማሳያ መሳሪያ ነው📖ይላሉ፡፡ በተጨማሪም ሰዋስው ሰዎች ቋንቋቸውን እንዲመሰረቱና እንዲተነትኑ የሚያስችል የአዕምሮ ስርዓትና ህግ ክፍል ነው በማለት ይበይኑታል፡፡

እንዲሁም እንደ Yashpal and Sunil, (2005:47) ገለጻ ሰዋስው የተለያዩ ስልታዊ ትርጓሜዎች አሉት፡፡

እነሱም:-

- ቃላትን በማዋሀድ ትርጉም ያለው መልዕክት የሚተላለፍበት፣
- የቋንቋ መዋቅሮችን የመግለፅ፣የመተንተንና የማሳውቅ ሂደት፣
- ሰዋስው የቋንቋን ህግና አመሰራረት የሚከተል ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

ሰዋስው ማለት እንደ ዘመናውያን የቋንቋ ምሁራን አገላለጽ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ሰዋስው የድምፅ አወቃቀርን እና የትርጉም ስርኣትን የያዘና ሁሉም የቋንቋው አፍ መፍቻ ተናጋሪዎች በቋንቋው እንዲግባቡና እዲረዳዱ የሚያስችል ነው ይሉታል (Brown, 2006)::

Rood, (2007፡8) በበኩላቸው ሰዋስው ማለት ስለ ቋንቋ የሚያጠና አካል ነው ሲሉ ያስገነዝባሉ:: አክለውም በተለመደው አገላለፅ ሰዋስው ማለት የቃላት ዕርባታና አነባብን ያጠቃልላል፡፡

እንደ ዘመናዊ የቋንቋ ምሁራን ገለፃ ደግሞ ሰዋስው ማለት የድምፀ ልሳናት ጥናት ቃላትን ለመፍጠር ትክክለኛ የድምፆች ድርድር፣የስነ-ፍች ጥናት እና ተግባራትን የሚያጠቃልል የጥናት ክፍል ነው ይሉታል፡፡

ባየ (2000፣13) ደግሞ ቀደም ባለው ጊዜ ስለ ሰዋስው የነበረው ግንዛቤ በሀረግና በዐረፍተ ነገር አመሰራረት፣ አይነት እና አገባብ ላይ ብቻ ስለ ሚያተኩር ውሱን እንደነበር ከገለፁ በኋላ በአሁኑ ጊዜ ግን በሀረግ እና በአረፍተ ነገር ብቻ ሳይወሰን የአንድን ቋንቋ ድምፅ አይነትና አቀነጃጀት እንዲሁም የቃላትን የአወቃቀር ስርዓት ይጨምራል፡፡ መሰላልነቱም ከድምፅ ጀምሮ እስከ አረፍተ ነገር ድረስ ላለው አጠቃላይ የቋንቋ ስርዓት ስለሆነ ያሁኑ የሰዋስው ግንዛቤ ከበፊቱ ሰፊ ነው በማለት ይገልፁታል፡፡

ጌታሁን (1990፣IV) በበኩላቸው በአሁኑ ወቅት ሰዋስው የሚለው ቃል ሁለት አሻሚ ፍችዎችን ይዞ ይገኛል፡፡ አንደኛው ፍች የሰው ልጅ የሚጠቀምበት ቋንቋ እውቀት የሚጠቀመውና በሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ ያለውን ችሎታ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ሰዋስው አዕምሮአዊ እሳቤ ነው ለማለት ይችላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ተመራማሪዎች ስለ ቋንቋ ስርዓትና መዋቀር የሚያደርጉትን ገለፃ የሚመለከት ስለሆነ ከመጀመሪያው ፍቺ ጠባብ ነው በማለት የሰዋስውን ምንነት ያብራሩታል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ስለ ሰዋስው ከተሰጠው ብያኔ የምንረዳው ቀደምት የቋንቋ ምሁራን ሰዋስውን የሀረግ፣ የአረፍተ ነገር አገባብ፣ አይነትና የቋንቋውን ህግ የሚያጠና እንደሆነ ሲገልጹ፣ በዘመናውያን የቋንቋ ምሁራን ዕይታ ግን የቋንቋውን ህግ እና ስርዓት ከማጥናት በአለፈ በሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ ያለውን የቋንቋ ችሎታ፣ ከድምፅ አፈጣጠር እስከ አረፍተ ነገር አደረጃጀት እና አጠቃቀም የሚያጠና የጥናት መስክ መሆኑን ያሰምሩበታል፡፡

Leech,(1994:19) ሰዋስው የተግባቦታዊ ክንውኖችን እና የክንውኖችን አውድና ትርጉም በአንድነት አጣምሮ በቀላሉ መረዳት የሚያስችል ነው በማለት አስፈላጊነቱን ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም Atkins,(1995) ሰዋስው ሰዎች በተቻለ መጠን መልእክትን በማቀናጀት በማንኛውም የተግባቦት ጊዜ ተግባቦቱን ውጤታማና የተቀላጠፈ ማድረጊያ መሳሪያ ነው ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡ ለዚህም ነው ቋንቋን የሚማር ሰው ሰዋስውን መማር አስፈላጊነቱ የጎላ የሚሆነው፡፡

ሰዋስውን መማር ደግሞ የአንድን ቋንቋ ምንነት ለመረዳት ማለትም ውስጣዊ አወቃቀሩን እና ከቋንቋው ህግጋት ውጭ የሆኑ ስህተቶችን ነቅሶ ለማየት ያስችላል፡፡ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ሰዋስዋዊ

እውቀት ሳይረዱ እንደሚግባቡበት ይታወቃል። ይሁን እንጂ የቋንቋቸውን ሰዋስዋዊ ህግጋት ማወቃቸው ተግባቦታቸውን ለማዳበር ከማገዙ ባሻገር ሁለተኛ ቋንቋን ለመማርም ዳራዊ እውቀት ሆኖ ያግዛል (Patel and Jain,2008)።

የሰዋስው ትምህርት ከላይ ከተገለፁት ጥቅሞች ባሻገር ለቋንቋ ክሂሎች መዳበርም አስተዋፅኦ አለው። የሰዋስው እውቀት ካለ በንግግርና በማዳመጥ ወቅት ፅንሰ ሐሳቡን በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስተላለፍ፣ በንባብ ጊዜም የንባቡን ፍሬ ነገር በቀላሉ ለመረዳት፣ በፅሕፈት ክሂልም ተገቢውን መልዕክት በትክክል ለማስፈር ያግዛል። አልፎ ተርፎም ለቃላት ትምህርት አስተዋፆኦ አለው። ይኸውም ቃላት በስርዓት ተቀናጅተው እንዴት ዐረፍተ ነገር እንደሚመሰረቱ ለመረዳት ያግዛል ሲሉ Widodo, (2006:122) ይገልፃሉ።

በአጠቃላይ የሰዋስው ትምህርት ግብ ተማሪዎችን የስነ-ልሳን ባለሙያ ማድረግ ባይሆንም አጠቃላይ የሆነውን የተግባቦት ችሎታቸውን ለማበልፀግ ትምህርቱ ማተኮር ይኖርበታል።ይህም የሚሆነው በክሂል ላይ ብቻ ሳይሆን በስርአትም ላይ ጭምር መሆን አለበት። ምክንያቱም ሁለቱም ችሎታዎች ተማርኩ ከሚል ሰው የሚጠበቁ ናቸውና (ጌታሁን፣ 1989)።

ስለሆነም የተማሪውን የቋንቋ አጠቃቀም የተሟላ ሊያደርገዉ የሚችል የሚጠቀምበትን ቋንቋ ስርአት ጠብቆ በአገባቡ ሲገለገል፣ የቋንቋውን ህግጋትና ባህሪያት ሲያውቅ ነው። ይህንንም የቋንቋ ስርአት እና ባህሪያት ተማሪው በአገባቡ ለመረዳት ይችል ዘንድ የሰዋስውን ትምህርት ማስተማር ተገቢና አስፈላጊ ተግባር ነው።

ይህ ጥናትም ትኩረት የሚያደርገው የዘመናዊ ሰዋስው ንድፈ-ሃሳብ አራማጆችን እሳቤ በመያዝ በታላሚ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን እና ስርአተ ነጥብን በተመለከተ በሙሉ መገምገም ነው።

ስነ-ድምፅን በተመለከተ በቃላት ውስጥ የድምፅ መጥበቅና መላላት፣ በቃል ውስጥ ያሉ ሆሄያትን ቦታ በመቀያየር የተለያዩ ቃላት መመስረት፣ እና በድምፅ ክትትሎሽ ሳቢያ የሚከሰቱ የድምፅ መዋጥ የሚሉ ናቸው።

ስነ-ምዕላድን በተመለከት፡ ቅጥያዎችን መለየት፣ቅጥያዎችን በዋና ቃል ላይ በመጨመር ቃላት መመስረት፣ማሰሪያ አንቀጽ ከሆኑ ቃላት የስም እና የግስ ገላጭ መመስረት፣ድርብ ቃላት መመስረት፣ምህፃረ ቃላትን መመስረት እና ከስማዊ ቃላት የስም ገላጮችን መመስረት የሚሉ ናቸው።

ስነ-አገባብን በተመለከተ፡ የሀረግ ምስረታ፣ ዐረፍተ ነገር ምስረታ፣ በቃላት ላይ ባሉ አፀፋዎች አማካይነት መደብን መለየት፣ ተፈጥሯዊ ጾታን መለየት፣ በዐረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ቃላትን ቦታ በመቀያየር የሚያመጡትን የፍች ለውጥ ማየት፣ የዐረፍተ ነገር ባለቤት እና ማሰሪ አንቀጽ በጾታ እና በቁጥር ማስማማት፣ ቃልን፣ ሀረግን እና ዐረፍተ ነገርን መለየት፣ የቃላት እና የሀረጋትን ቦታ መለዋወጥ እና መተካት፣ የስም ገላጮችን መለየት፣ የግስ ገላጮችን መለየት፣ የተዘበራረቁ ቃላትን ቅደም ተከተል በማስያዝ የተስተካከለ ዐረፍተ ነገር መመስረት፣ የሰዋስው ግድፈት ያለባቸውን አረፍተ ነገሮች አስተካክሎ መጻፍ፣የተጓደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በተገቢ ቃላት ማሟላት፣ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣የዐረፍተ ነገር ስልቶች፣ በዐረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ሙያ መግለፅ፣ ከረጃጅም ዐረፍተ ነገሮች አጫጭር ዐረፍተ ነገሮች መመስረት፣ ገለጮችን በመጨመር ዐረፍተ ነገርን ማጎልበት እና የዐረፍተ ነገር አይነቶችን መግለጽ ናቸው።

ስነ-ፍችን በተመለከተ ደግሞ የቃላት እማሬያዊ ፍች፣ የቃላት አውዳዊ ፍቺ፣ የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ፣ የቃላት ተቃራኒ ፍቺ፣ በፍቺ የተለየውን ቃል መምረጥ እንዲሁም የሀረግ ፍቺ፣ የሀረግ አውዳዊ ፍቺ፣የሀረግ ተመሳሳይ ፍቺ እና የዐረፍተ ነገር ተመሳሳይ ፍቺ የሚታዩ ስለሆነ እነዚህን ይዘቶች ደግሞ ሊያካትታቸው የሚችለው የዘመኑ የስነ ልሳን ምሁራን የሰጡት አስተያየት ነው።

## 2.2. የሰዋስው ይዘቶች አመራረጥ

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አቀራረብና መገምገሚያ መስፈርቶችን በተመለከተም ብዙ ምሁራን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ከዚህ ውስጥ Stervens,(1983),Harmer,(1987),እና Swan,(1994) እንደሚሉት፣ ትክክለኛነት፣ ግልፅነት፣ ተገቢነትና ተመጣጣኝነት ወይም ሚዛናዊነት የሚሉት በመስፈርትነት የሚጠቀሱ ናቸው።

በአብነት ያህል የትምህርት አላማን ለማሳካት የሚመረጡ ልምዶች መያዝ ያለባቸውን ባህርያት Stervens,(1983)ሲገልፁ፣የትምህርት ልምዶች የታለመውን አላማ ግብ ያስመቱ ዘንድ እውነተኛ፣ተገቢ፣አዝናኝ፣አበረታች እና ተጣጣሚ መሆን አለባቸው ይላሉ። Swan, (1994:45-53) በበኩላቸው መስፈርቶችን ትክክለኛነት፣ ግልፅነት፣ ተገቢነት እና ገደብ ሲሉ Harmer, (1987:18-19) ደግሞ ግልፅነት፣

ትክክለኛነት፣ ሚዛናዊነት እና ተገቢነት ናቸው ይላሉ። ይህ ጥናትም የሚያተኩረው በታላሚ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶችን ግልጽነት፣ ትክክለኛነት፣ ሚዛናዊነት እና ተገቢነት ማየት ነው።

## **2.2.1.** ትክክለኛነት

ትክክለኛነት በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚካተቱ የትምህርት ይዘቶች የቋንቋውን ትክክለኛ ስነልሳናዊ ባህሪ የሚያሳዩ መሆናቸውን የሚጠቁም ፅንሰ ሀሳብ ነው። ይኸውም የቋንቋው ተጠቃሚ ማህበረሰብ በሚገለገልበት አኳኋን መቀመጥ ያለበት መሆኑን Swan, (1994:46) ያስገነዝባሉ። እውነተኛነት (ትክክለኛነት) ሲባልም መጽሐፉ ተማሪው ከበቀለበት አካባቢ እና ከገሀዱ አለም ጋር መስማማት እንዳለባቸው የተሰነዘረ ሀሳብ መሆኑን Stervens, (1983፡71) ያስገነዝባሉ።

በአጠቃላይ በቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ትክክለኛ እና እርግጠኛ ሊሆኑ ይገባል። የሚመረጡ ይዘቶችም የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግጋት የማያፋልሱ መሆን አለባቸው። ትክክለኛነት ግልፅነትን ያጎናፅፋል። ምክንያቱም ለመማር ማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች የተፈተሹና የተረጋገጡ በሆኑ ቁጥር ተማሪዎች መልመጃዎችን ለመስራት መምህራንም ለማሰራት እጅግ ግልፅ ይሆንላቸዋል። ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ መልመጃዎችም ሆኑ መመሪያዎች ግልፅና ትክክለኛ አቀራረብ ይዘው ሊቀርቡ እንደሚገባ ከገለፃው መረዳት ይቻላል።

## 2.2.2. ግልፅነት

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚካተቱ ይዘቶች ተማሪውን የማያደናግሩ እና ያልተደባበሱ ወይም ግልፅ ሊሆኑ ይገባል ሲሉ Stervens, (1983፡71) ይገልፃሉ። Swan, (1994:48) በበኩላቸው በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ግልፅ ሊሆኑ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

ይህም በአገባቡ ይሳካ ዘንድ የትምህርት ይዘት አደረጃጀቶች ተገቢውን ቅደም ተከተል የጠበቀ አብነቶችን የያዘ፤ ትኩረት ለሚገባቸው ነጥቦች አፅንኦት የሰጠ፤ አሻሚነትን ያስወገዱ ሊሆኑ እንደሚገባቸው ያሳስባሉ።

በጥቅሉ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ አብነቶች፣ ትእዛዞች እና ይዘቶች ግልፅ በሆነ መልኩ መቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ተማሪው ያለማንም አጋዥ መማሪያ መጽሐፍፉን አንብቦ ተረድቶ ተገቢውን ልምድ ለመፈፀም እገዛ ስለሚያደርግለት ነው።

### 2.2.3. ተመጣጣኝነት

ይህ የሚያመለክተው በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶች ሽፋን ወይም ስርጭት ተቀራራቢ መሆን እንዳለበት ነው። ማለትም የቋንቋውን የክሂል ዘርፎች፣ የስነፅሁፍ እና የሰዋስዋዊ ይዘቶች ተመጣጥነው መቅረብን የሚመለከት ነው። ምንም እንኳ ከትምህርት ይዘቶች ውስጥ ውስብስብ ለሆነው የበለጠት ኩረት ሊሰጥ ቢችልም በተቻለ መጠን ሁሉም ባልተራራቀ መልኩ የሚዳስስ መሆን አለበት። በዚህ መልኩ የይዘት ስርጭትን ፍትሀዊነት ጠብቆ የተደራጀ የመማሪያ መጽሐፍ የተማሪዎችን የክሂልም ሆነ የእውቀት ዘርፎችን በአግባቡ ያሳድጋል። የመማር ማስተማሩን ሂደትም ከአሰልችነት ይታደጋል።

ስለሆነም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዲሁ ከስነ-ድምፅ፣ ከስነ-ምእላድ፣ ከስነ-አገባብ እና የስነ-ፍች ስርአትም በተውጣጣ ወይም በአካተተ መልኩ ሊደራጁ ይገባል (Tonkyn,1994) , (Harmer,1987:19)።

### 2.2.4. ተገቢነት

በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚኖር የይዘት ተገቢነት ከተማሪው አላማ፣ እድሜ እና እንዲያሳይ ከሚጠበቅበት የባህሪ ለውጥ ጋር ተጣጥሞ መቅረብ አለበት ሲሉ Stervens, (1983፡71) ያስገነዝባሉ። ተገቢነት ከተማሪው የመስራትና የማገናዘብ አቅም ጋር የሚፈረጅ ሲሆን ለትምህርት የተመረጡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የተማሪውን እድሜ፣ ገጠመኝ፣ የክፍል ደረጃ፣ ፍላጎት እና ዝንባሌ መሰረት ሊያደርግ እንደሚገባ Swan,(1994:51) ያስረዳሉ። ሌላው Harmer,(1987: 21) የይዘት ተገቢነትን ሲገልፁ በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ይዘቶች ለቋንቋ ትምህርት አላማ መሳካት አስተዋፅኦ አኳያ የሚታይ መሆኑን ይገልፃሉ።

ተገቢነት በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገበት በመማሪያ መጽሐፍ እና በመርሃ ትምህርቱ መካከል ያሉ የሰዋስው ልዩነቶችን መመልከት ነው።

## 2.3. የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀት

በብዙ ምሁራን የታመኑባቸው የሰዋስው የትምህርት ይዘቶች የአደረጃጀት መርሆች ወይም ስልቶች የሚከተሉት ናቸው።

## 2.3.1. ተከታታይነት

ተከታታይነት በአንድ የትምህርት አይነት የተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች ይዘት ወይም የትምህርት ልምድ ተደጋግሞ መከሰቱን የሚያሳይ ነው ሲሉ Tyler,(1949:84) አስገንዝበዋል። ተስፋዬ (1981፡40) በበኩላቸው ተከታታይነት በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚመጣጠን ይዘት እንደሚመለከት ገልፀዋል።

በአጠቃላይ ከቀረበው ገለፃ የምንረዳው ተከታታይነት አንድ ይዘት በአንድ ክፍል በተለያዩ ምዕራፎች ተደጋግሞ ሊቀርብ እንደሚችል የሚያስገነዝብ ነው። ይህም ተማሪዎች አንድን ይዘት በቀደመው የትምህርት ይዘት እውቀታቸው ተመስርተው የበለጠ ለመረዳትና ለማስታወስ ይመቸዋል። ያልተረÄ*ቸውንም ለመረዳት ተጨማሪ አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል።

### 2.3.1.1. የሰዋስው ትምህርቶች ይዘትና አቀራረብ

#### 2.3.1.1.1. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር

በዚህ አቀራረብ ስልት ተማሪዎች ስለሚማሩት የቋንቋ ህግ የሚያስረዳ ትንተኔ ይቀርብላቸዋል በሚቀርብላቸው ትንታኔ መሰረት የተሰጣቸውን ልዩ ልዩ መልጃዎች በመስራት ወደ ህግጋቱ ይደርሳሉ/ ይማራሉ። (Patal and Jain, 2008), (Yasphal and Sunit, 2005) ይህ አቀራረብ እውቀት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ይመነጫል ከሚለው አስተሳሰብ የተነሳ ነው። በዚህ አቀራረብ ስልት መሰረት ህጎች፣መርሆች፣ፅንሰ ሀሳቦች ወይም መላምቶች ይቀርባሉ። ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብና Stern, (1992) በሚከተለው መንገድ አብራርተዋል።

ህግጋትና ደንቦች ⟶ ጥልቅ ምሳሌዎች ⟶ መልመጃዎችን መስራት

ሌላው ሰዋስው በማስተማር ዙሪያ ይህ አቀራረብ በህግ የተመራ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። በመጀመሪያ ለተማሪዎች ሰዋስዋዊ ህጉ ይነገራቸዋል ከዚያም የራሳቸውን ምሳሌ በመመርመር ይማራሉ Widodo,(2006፡126) አክለውም Swan,(1999፡32) በመጥቀስ የሰዋስው ይዘቶች ከአጠቃልይ ወደ ዝርዝር ሲቀርቡ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ነጥቦች ሊታሰቡ ይገባል።

- ሰዋሰዋዊ ህጎች እውነት ሊሆን ይገባል።
- ሰዋስዋዊ ህጎች አንድን የተወሰነ መማሪያ መጽሐፍም የህግ ገደብ በግልፅ ሊያሳዩ ይገባል።
- ሰዋስዋዊ ህጎች ግልፅ ሊሆን ይባላል።

- የሚቀርቡ የሰዋስው ህጎች ቀላል ሊሆን ይገባል፡፡
- ሰዋስዋዊ ህጎች ተማሪዎች ከሚያቁት እና ከሚቀሙበት ፅንሰ ሀሳብ መነሳት አለባቸው፡፡
- ሰዋስዋዊ ህጎች ጠቃሚ እና ተጨባጭ መሆን አለባቸው፡፡

### 2.3.1.1.2. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ

ይህ አቀራረብ አመጣጡ ማንኛውም አስተሳሰብና እድገት ከትንሽ ወደ ትልቅ ያደገ ነው ከሚለው እሳቤ የመነጨ ነው፡፡ ይህም ምልክቶችና ስልቶችን ህገ ደንቦችን እና ፅንሰ ሀሳቦችን ሲጨምር ይችላል Felder and Henriques, (1995) ይገልፃሉ ሲተገበር ከምሳሌ ወደ አጠቃላይ በሚል ንድፍ ሀሳብ መሰትነት ነው፡፡ Thornbury, (1999) አክለው ሲገልፁ ተማሪዎች የአንድን የሰዋስው ህግ እና ደንብ ከምሳሌው በመነሣት ሳያስቡትና ሳይጨነቁ እንዲያውቁ እንደሚለዩ ያስገነዝባሉ፡፡ Ruterford, (1987፡5) በበኩላቸው እንደገለፁት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ስምሰራን በተወሰኑ የሰዋሰው ህግጋት ላይ ገለፃ ሳያደርጉ ተማሪዎች ለራሳቸው ህግጋቱን እንዲለዩላቸው የሚያግዝ የሰዋስው ማስተማሪያ ስልት ነው ሲሉ ያስገነዝባሉ፡፡ እንዲሁም Ellis, (1992) ስለ አቀራረቡ ሲገልፁ ተማሪዎች ከተሰጠው ምሳሌና አውድ በመነሳት የሰዋስው ህግጋትን እንዲለዩ ሀላፊነት መስጠት ነው፡፡ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ Stern,(1997) ከሚከተለው መልስ ያጠቃልሉታል፡፡

ጥልቅ ምሳሌዎች → ምልመጃዎች መለማመጃ → ህግጋት እና ደንቦች ላይ መድረስ

### 2.3.2. ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት ከተከታታይነት ጋር የሚዛመድ ፅንሰ ሃሳብ ያለው ነው፡፡ ይኸውም በትምህርትነት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርቡ የትምህርት ልምዶች በድጋሜ በቀጣዩ ክፍል ሲቀርቡ ስፋትና ጥልቀት እያገኙ መሄድ እንዳለባቸው የሚያስገነዝበን ነው ተስፋዬ (1981፡41) ፡፡ ይህም ማለት አንድ የትምህርት ይዘት ቀደም ከቀረበበት ቀጣይ ክፍል በድጋሚ ሲቀርብ ከበፊቱ የበለጠ ስፋትና ጥልቀት ሊኖረው እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

Tyler,(1949:84) ተለጣጣቂነትን ሲገልፁ:- ተለጣጣቂነት በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኝ አይደለም፡፡ ይልቁንም አንድ የትምህርት ይዘት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ተደጋግሞ መምጣትን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም ሲሆን በድግግሞሹ የሚቀርቡ ይዘቶች ጥልቀታቸው እየጨመረ መሄድ እንዳለበት ያስገነዝባሉ፡፡ Nunan, (1988)

በበኩላቸው ተለጣጣቂነትን የቋንቋ የትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነት ባለው መልኩ እርስ በእርስ ተሰናክለው መደራጀት እንዳለባቸው የሚያሳይ እንደሆነ ያስገነዝባሉ። ይኸውም አንድ የትምህርት ይዘት በድጋሚ ሲቀርብ ከክፍል ወደ ክፍል እያደገና ጥልቀቱ እየጨመረ መሄድ እንዳለበት እንገነዘባለን።

በአጠቃላይ ተለጣጣቂነት ከተከታታይነት ጋር የሚጋራው ነገር ቢኖርም ይዘቶቹ ከምዕራፍ ምዕራፍ ወይም ከክፍል ወደ ክፍል ስፋት እና ጥልቀትን እያገኘ ተደጋግሞ መምጣቱን የሚያመለክት እንደሆነ ከምሁራኑ ገለፃ እንረዳለን።

የሰዋስው ህጎችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ወይም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ከሚሉ አቀራረቦች በየትኛው ብናስተምር ይሻላል የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ የተወሰነ የተወሰነ የቋንቋ ቅርፅና ግምት ያስገባ ሊሆን እንደሚገባ ይገልፃሉ። በተጨማሪም ምክንያቱን ሲገልፁ እያንዳንዱ አረፍተነገሮች ተለጣጣቂ ሆነው ሲማሩ ተማሪዎች ውጤታማ ሲሆን እያንዳንዶቹን የቋንቋ ይዘቶች ደግሞ ከዝረዝር ወደ አጠቃላይ ተለጣጣቂ በማድረግ ማስተማር የቋንቋውን ሰዋስው ተማሪዎች በአግባቡ እንደተዋወቁ ያደርጋል ሲሉ Eisenstein, (1987) እና Brown, (2005) ያስገነዝባሉ።

በአጠቃላይ በርካታ ምሁራን የሰዋስው ይዘትን ተለጣጣዊነቱን ጠብቆ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የማስተማር አቀራረቦች ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ሊኖሩትም እንደ Tudor, (1996:211) ገለፃ አንድም ወይም የትኛውም የሰዋስው ማስተማሪያ አቀራረብ ለሁሉም ተማሪዎች በእኩል ደረጃ የሚስማማና የሚመች አይደለም።

ስለዚህ መምህራን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ወይም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ ዘዴዎችን ተለጣጣቂነታቸውን ጠብቀው ማስተማር አለባቸው ሲሉ ይገልፃሉ።

## 2.4. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ሐዋዝ (2000) "በአዲስ አበባ ከተማና በአማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ንፅፅራዊ ጥናት'' በሚል ርእስ የቀረበ ጥናት ነው። የጥናቱ ትኩረት በ1997 ዓ.ም. በተሸሻሉት የአዲስ አበባ መስተዳድርና የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ተማሪዎች በሚጠቀሙባቸው የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ እና አደረጃጀትን በማነፃፀር ተመሳስሎና ልዩነታቸውን ነቅሶ በማውጣት ላይ ያተኮረ

ነው። የጥናታቸውን አላማ ከግብ ለማድረስ የተጠቀሙባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችም የሰነድ ፍተሻ፣ቃለ መጠይቅና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው።

በግኝታቸውም ሁለቱም ክልሎች በአንድ መርሃ ትምህርት ላይ ተመስርተው ባዘጋጁቸው የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስውን ትምህርት ከማቅረብ አንፃር የአደረጃጀት እና የአቀራረብ መርሆዎችን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ጠንካራ ጎን አላቸው። ይሁን እንጂ ከተጠቀሱት ጥንካሬዎች ውስጥም መለስተኛ የሆኑ ልዩነቶች እና ድክመቶች መታየታቸውን አብራርተዋል። ልዩነቶችም የትኩረት፣ የመርህ ምርጫ ወይም መርሃ ትምህርቱን በተሟላ መልኩ መከተል ያለመቻል ወይም ለየት የማለት ሲሆን ከድክመቶች ውስጥም የፅንሰ ሃሳብ፣ የአርትኦት ወይም የአደረጃጀት መርሆችን የመተግበር፣ እጥረቶች መሆናቸውን ገልፀዋል።

እስሌማን (2003) “በ12ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት እና አቀራረብ’’ የሚል ነው። የጥናታቸው ዋና አላማም በ1998 ዓ.ም. ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት እና አቀራረብ ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስዋዊ መርሆች አንጻር መፈተሽ ነው። የጥናታቸውን አላማ ከግብ ለማድረስ የተጠቀሙባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሰነድ ፍተሻ፣ቃለ መጠይቅ እና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው።

በግኝታቸውም መሰረት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ዝምድና የሌላቸው ሆነው መገኘታቸውን ገልጸዋል። ከሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት አንጻር ደግሞ ጥሩ ገጽታ እንዳላቸው አስገንዝበዋል።

ዮሐንስ (2003) “በትግራይ ክልል ለ9ኛ እና ለ10ኛ ክፍል በተዘጋጁት የትግርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አቀራረብ እና አደረጃጀት ግምገማ’’ የሚል ርዕስ ነው። የጥናቱ ዋና አላማም በታላሚ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አቀራረብ እና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል መገምገም ነው። የጥናታቸውን አላማ ከግብ ለማድረስም የተጠቀሙባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች የሰነድ ግምገማ እና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው።

በግኝታቸው መሰረት ታላሚ መጽሐፍቱ በውስጣቸው የያዟቸው የሰዋስው ይዘቶች ከአመራረጥ፣ ከአቀራረብ እና ከአደረጃጀት መርሆዎች አንጻር መጠነኛ ችግር እንዳለባቸው ገልፀዋል።

ባዩ (2004) “በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ’’ የሚል ርእስ ሲሆን ትኩረታቸውም የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ነው። የጥናታቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ስልትም በዋናነት የሰነድ ምርመራ ሲሆን የፅሁፍና የቃለ መጠይቅ በአጋዥነት ተጠቅመዋል።

በግኝታቸውም መሰረት በአራቱም የእርከኑ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት እንከን እንዳለባቸው ጠቅሰዋል።

በልዩ ልዩ ጊዜያት የታተሙ በርካታ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን የገመገሙት ሌላው አጥኚ እምሻው (2005) ናቸው። የጥናታቸው ርዕስም “ለ9ኛ እና ለ10ኛ ክፍል ከ (1968-2004 ዓ.ም) በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ’’ የሚል ነው።

የጥናታቸው አብይ አላማም ከ1968- 2004 ዓ.ም ድረስ ለ9ኛ እና ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ያገለገሉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በመገምገም ያሳዩትን ለውጥ መፈተሽ ነው። በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀሙት የሰነድ ምርመራን ነው።

ያገኙት ውጤትም በተተኳሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ገፅታ የተለያየ ቢሆንም ታላሚዎቹ መጽሐፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻልና ለውጥ ያሳዩ መሆኑን ገልፀዋል። ቢሆንም ግን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር አቀራረብን አመጣጥኖ ከማቅረብ አኳያ መጽሐፍቱ ሙሉ በሙሉ ከችግር ያልፀዱ መሆናቸውን አጥኚው አረጋግጠዋል።

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት አጥኚዎች የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶቻቸውን ሰዋስውን ተተኳሪ በማድረግ ለተለያዩ ክፍሎች ማስተማሪያ በተዘጋጁ ልዩ ልዩ የመማሪያ መጽሐፍ ላይ ጥናት አከናውነዋል፤ የታዩ እንከኖችን በመጠቆም እንዲስተካከሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን ሰጥተዋል። ከተጠቀሱት ጥናቶች ከእምሻው በስተቀር ሌሎች በአንድ ወቅት በአገልግሎት ላይ የነበሩ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የገመገሙ ሲሆን፤ እምሻው ግን ከ1968 - 2004 ዓ.ም በተከታታይ ጊዜያት ከ9ኛ-10ኛ ክፍል ለማስተማሪያነት የተዘጋጁ ከአገልግሎት በኋላና በአገልግሎት ላይ ያሉ መጻህፍትን ገምግመዋል።

የአንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀት እና አቀራርብ በሚመለከት ግን አገልግለው ያለፉትን እና በማገልገል ላይ ያሉትን በማነፃፀር የተሠራ ጥናት አላጋጠመኝም::

ከ2ኛ ደረጃ መማሪያ በተለየ የአንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሚዘጋጁት በክልል ደረጃ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ በክልል ደረጃ የተሄደበት መንገድ እና የተገኘው ልምድምን እንደሆነ ለማወቅ አይቻልም::

ስለዚህም ለሰባተኛ እና ለስምንተኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያነት ተዘጋጅተው እያገለገሉ የሚገኙ የተማሪ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ እና አደረጃጀት የለውጥ ሂደቱን ነቅሶ በማሳየት በዚህ ረገድ ያለውን ክፍተት መሙላት ዋነኛ አነሳሽ ጉዳይ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

## 3.1. የጥናቱ ዘዴ

አንድ አጥኚ ጥናቱ የሚያስፈልጉት መረጃዎችን ትክክለኛ እና አስተማማኝ በሆነ ዘዴ ከሰበሰበ በኋላ አግባብ ያለው የትንተና ዘዴ መርጦ መጠቀም እንደሚገባው ይታወቃል። አንድን ጥናት ከግብ ለማድረስ ሁለት ዓይነት የመተንተኛ ዘዴዎች ሲኖሩ እነርሱም መጠናዊ እና አይነታዊ የትንተና ዘዴዎች ናቸው።

መጠናዊ የሚባለው በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ይዘቶችን በልዩ ልዩ ስታስቲካዊ የቀረቡትንም ሆነ ስታስቲክስ አልባ የቀረቡትን በገለፃ እና በሃተታ የሚያብራራ ነው። ይህን ጥናትም ከግብ ለማድረስ መጠናዊ እና አይነታዊ የትንተና ዘዴ ተገቢ ተደርጎ በአጥኚው ተመርጧል።

እነዚህን የመረጃ መተንተኛ አጥኚው ለጥናቱ ታአማኒነት እና ትክክለኛነት ሲል የመረጣቸው ዘዴዎች ከመሆናቸውም በላይ መጠናዊ ዘዴ ሊመረጥ የቻለበት በሰነድ ፍተሻ የሚሰበሰበውን መረጃዎች አህዛዊ ሆነው ሲገኙና የተገኙትን መረጃዎች የሚለካቸው ወይንም እንዲለኳቸው የሚፈለጉት በጥንቃቄ ለይቶ ለማጥናት ስለሚረዳ በአጥኚው ሊመረጥ ተችሏል።

በሌላ በኩል የተሰበሰቡትን መረጃዎች በገለፃ፤ በትረካ እና በማብራሪያ መልክ የሚተነተኑበት የመረጃ መተንተኛ መንገድ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴም ስለሆነ ተመራጭ ሊሆን ችሏል።

በጥቅሉ አይነታዊ እና መጠናዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ያስችል ዘንድ በአጥኚው የታመነባቸው የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ናቸው።

## 3.2. የመረጃ ምንጮች

የዚህን ጥናት አብይ የመረጃ ምንጭ የሚያገለግሉ የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል የተማሪው መጻህፍት ነው። እንዲሁም ለታላሚው መጽሐፍ ተግባራዊነት እና በውስጣቸው የያዙዋቸውን የተለያዩ የትምህርት ዓላማዎችን አቅፎ የያዘውን የታላሚ ክፍሎች መርሃ ትምህርት በመረጃ ምንጮነት የሚያገለግሉ ናቸው።

ጥናቱ የሚከናወነው የሰዋስው ትምህርት ይዘት አመራረጥ እና አደረጃጀትን በመመርመር ላይ ስለሆነ ከተተኳሪ መጽሐፍ ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ተለቅመው ከወጡ በኋላ ምን አይነት ይዘት እና አደረጃጀትን በሚመለከት ስለሆነ ታላሚ መጽሐፍ እና መርሃ ትምህርታቸው ለጥናቱ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል የተማሪዎች ማስተማሪያ መጻህፍት ጥናቱ የሚከናወንባቸው ምንጮች ናቸው፡፡ የታላሚዎቹን መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አመራረጥ እና አደረጃጀትን በሰነድ ፍተሻ በመታዘዝ መረጃዎች ይተነተናሉ፡፡ ስለዚህ ይህንን ዓላማም ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ በአጥኚው የታመነበት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሰነድ ፍተሻ ዘዴ ነው፡፡

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የተመረጠበት ምክንያትም ከላይ እንደ ተጠቀሰው ሁለቱ ታላሚ መጽሐፍ ከታቀደው ዓላማ አንፃር ለመገምገም ያስችል ዘንድ የታላሚዎቹን የመማሪያ መጽሐፍ ሰዋስው ይዘት አመራረጥና አደረጃጀትን መፈተሽ አስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡

በተጨማሪም የመርሃ ትምህርቱ ዓላማ እና ይዘት ከታላሚ ክፍል ተማሪዎች ጋር መጣጣሙንና አለመጣጣሙን ብሎም ሰዋስው ይዘቱ ለታላሚው ክፍል የትምህርት ደረጃ የሚመጥን መሆኑን ለማወቅ ያስችል ዘንድ ሰነድ ፍተሻ ተመራጭ ሆኗል፡፡

## 3.4. የመማሪያ መጽሐፍ የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ ለጥናቱ መነሻ በመሆን የተመረጡት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል የአማርኛ ቋንቋ የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል የመማሪያ መጻህፍት ናቸው፡፡

አጥኚው በታላሚው ዘመን ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው ሳይክል ማስተማሪያ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ይዘት እና አደረጃጀትን ትኩረት በማድረግ እንዲመርጥ አስችሎታል፡፡

## 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥእና አደረጃጀት አንፃር ቅኝት ይደረጋል፡፡ ታላሚው የመማሪያ መጽሐፍ በውስጣቸው ያካተቷቸው የሰዋስው

ይዘቶች በየክፍል ደረጃቸው ቅደም ተከተል መሰረት ተለቅመው ከቀረቡ በኋላ ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ እና አደረጃጀት መስፈርቶች አኳያ ይገመገማሉ፡፡

መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ አግባብ ያለው የትንተና ዘዴ መርጦ መጠቀም እንደሚገባ ከላይ በመግቢያው ላይ ተጠቁሟል፡፡ ይህን ጥናት ተግባራዊ ለማድረግ መጠናዊ እና አይነታዊ የትንተና ዘዴዎች በመጠቀም ከሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡትን መረጃዎች አህዛዊ ሆነው ሲገኙ በመተንተን የተገኙትንም መረጃዎች በአንቀፆች ይብራራሉ፡፡

ይህም ሲባል የተሰበሰቡትን መረጃዎች በገለጻ እና በማብራሪያ መልክ ስለሚተነትኑ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ እና መጠናዊ መተንተኛ ዘዴዎች ተመራጭ ሆነዋል፡፡ መጠናዊ ሲባል በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ይዘቶችን በመቶኛ መተንተን ተግባራዊ ለማድረግ ከማስቻሉም በላይ በሰነድ ፍተሻ ወቅት የሚገኙትን አህዛዊ መረጃዎችን በመጠን ለመግለጽ ያስችል ዘንድ ለጥናቱ አህዛዊ ልዩነት ለማሳየት ሲባል የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አጥኚ የሚጠቀመው ይሆናል፡፡

በሁለተኛነት በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ በሰነድ ፍተሻ ወቅት የሚቀርበው አይነታዊ የትንተና ዘዴ በመጠቀም ይሆናል፡፡ አይነታዊ የትንተና ዘዴ በዚህ ጥናት ውስጥ መጠቀም ያስፈለገው ምክንያት በመጠናዊ የትንተና ዘዴ የተገኙትን ስታስቲካዊ የጥናቱ ግንኙነቶችም ሆነ ስታስቲካዊ አባል ግኝቶችን በሃተታ ስለሚቀርቡ መጠናዊ የትንተና ዘዴን መሰረት በማድረግ የተገኙት ስታስቲካዊ መረጃዎችን ይበልጥ ይብራራሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

## 4.1. ስለ መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ መረጃ

በዚህ ርዕስ ተተኳሪ የሆኑት የ7ኛእና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መጻህፍት አጠቃላይ መረጃ ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ 1 የቀረበ ሲሆን በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት አጠቃ**ላ**ይ የሰዋ**ስ**ው ይዘቶች በሠንጠረዥ 2 እና በሠንጠረዥ 3 ተጠቃለው ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 1. የታላሚ መማርያ መጽሐፍ አጠቃላይ መረጃ

| መረጃዎች | የክፍል ደረጃ | |
|---|---|---|
| | 7ኛ | 8ኛ |
| የህትመት ዘመን | 2007 | 2007 |
| የገጽ ብዛት | 237 | 255 |
| የምንባብ ብዛት | 10 | 10 |
| የመልመጃዎች ብዛት | 360 | 422 |
| የሰዋስው ይዘቶች /መልመጃዎች/ብዛት | 30 | 30 |
| ዋጋ | 34.90 | 37.00 |

### 4.1.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

ሠንጠረዥ 2. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይዘት

| የክፍል ደረጃ | ገጽ | ርዕስ | የሰዋስው ይዘት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ስነ-ድምጽ | | ስነ-ምዕላድ | | ስነ-አገባብ | | ስነ-ፍቺ | | ድምር | |
| 7ኛ | ብዛት | ብዛት | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| | 237 | 10 | 2 | 6.7% | 9 | 30% | 11 | 36.7% | 8 | 26.7% | 30 | 100% |

ከላይ በሰንጠረዥ 2. ለመረዳት እንደምንችል የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ 237 ገጾች ይዞ 10 የተለያዩ ርዕሶችን የያዘ መጽሐፍ ነው። በነዚህ የተለያዩ ርዕሶች ስር30 የሚሆኑ የሰዋስው ይዘቶች የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ማካተቱን ለማየት ተችሏል። መማሪያ መጽሐፍ በውስጡ ካካተታቸው የተለያዩ የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ የስነ-ድምዕ ብዛት 2፣ ስነ-ምዕላድ ብዛት 9፣ የስነ-አገባብ ብዛት 11፣ እንዲሁም የስነ-ፍቺ ብዛት ደግሞ 8፣ በንዑስ ይዘትነት ይዟል። እነዚህ ንዑስ ይዘቶችም በመቶኛ ሲሰላ ስነ-ድምፅ 6.7%፣ ስነ-ምዕላድ 30%፣ ስነ-አገባብ 36.6% እና ስነ-ፍቺ 26% እንደሆነ ከሰነድ ፍተሻው ለማረጋገጥ ተችሏል።

## 4.1.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

ሠንጠረዥ 3. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይዘት

| የክፍል ደረጃ | ገጽ | ርዕስ | የሰዋስው ይዘት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ስነ-ድምጽ | | ስነ-ምዕላድ | | ስነ-አገባብ | | ስነ-ፍቺ | | ድምር | |
| 8ኛ | ብዛት | ብዛት | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| | 255 | 10 | 2 | 6.7% | 11 | 36 | 9 | 30% | 8 | 26.6% | 30 | 100% |

ከላይ ከሰንጠረዥ 3. ለመረዳት እንደምንችል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ 255 ገፆች ይዞ የተለያዩ ርዕሶችን ይዟል። በነዚህ ርዕሶች ስር 30 የሰዋስው ይዘቶችን ያካተተ የመማሪያ መጽሐፍ ለመለየት ተችሏል። በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከያዛቸው የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ የስነ-ድምጽ ብዛት 2፣ የስነ-ምዕላድ ብዛት 11፣ የስነ-አገባብ ብዛት 9፣ እንዲሁም የስነ- ፍቺ ብዛት ደግሞ 8 የሚሆኑ ንዑስ ሰዋስው ይዘቶች በታላሚው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አሰባጥሮ ይዟል። እነዚህ ሰዋስዋዊ ንዑስ ይዘቶች በመቶኛ ተሰልተው አጠቃላይ ሽፋናቸው ሲገለጽ ስነ-ድምጽ 6.7%፣ ስነ-ምዕላድ 36.7%፣ ስነ-አገባብ 30% እና ስነ-ፍቺ 26.6% እንደሆነ የሰነድ ፍተሻ ውጤት ያሳያል።

## 4.2. በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ አንፃር

መርሃ ትምህርት የመማር ማስተማሩን ስራ ውጤታማ ለማድረግ የሚረዳና ሁኔታዊ፣ ተግባራዊ፣ መዋቅራዊና የተለያዩ የቋንቋ ክህሎቶችን አካቶ የያዘ መሆን እንዳለበትና ይህን የቋንቋ መርሃ ትምህርት ለተግባራዊነት ለማቅረብ በሚዘጋጁበት ጊዜ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ነገሮች መርሃ ግብሩ፣ መምህሩ፣ ተማሪው እና ሌሎች ተዛማጅ ነገሮች እንደሆኑ ይታወቃል። እንዲሁም መርሃ ትምህርት ሲዘጋጅ ልንከተላቸው የሚገቡ መርሆች ማለትም በመዋቅራዊ ሰዋስው ተኮር ቋንቋን ማስተማር እንደሚችል በተጨማሪም የቋንቋን ክህሎቶች በማዋቀር ማስተማር እንደሚቻል እና በተማሪው ላይ የሚፈለገውን አዎንታዊ ለውጥ ማጎናፀፍ ይቻላል።

በጥቅሉ የቋንቋ መርሃ ትምህርት ዝግጅት የተለያዩ ይዘቶችን በማቀፍ እንዲሁም የሚፈለገውን የትምህርት ዓላማ በተቀናጀ መልኩ ተቀርፆ ለተማሪው እና ለመምህሩ ሊቀርቡ ይገባል። ምክንያቱም የተቀናጀ መርሃ ትምህርት ዝግጅት ለታቀደለት ስራ ውጤታማነት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ልብ ሊገባ ይገባልና ነው።

ከላይ በዝርዝር ከቀረበው መርሃ ትምህርት አወቃቀር እና ዝግጅት አኳያ ለአማርኛ መማሪያነት እያገለገሉ የሚገኙትን የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ አንፃር በሚከተሉት ንዑስ ርዕሶች ስር ተዳስሷል።

### 4.2.1. የመማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ ይዘት ከግልጽነት አንፃር

የአንድ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አመራረጥን ጠንካራ ከሚያስገኙት መርሆች ውስጥ አንዱ ግልፅነት ነው። ይህም ሲባል በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚካተቱ የሰዋስው መልመጃዎች እንዲሁም ለመልመጃ ስራነት የሚቀሪቡት ሰዋስዋዊ ምሳሌዎች ብዥታን በማይፈጥር መልኩ ግልጽ ሆነው ለተማሪው መቅረብ እንዳለባቸው በምዕራፍ ሁለት ስር ተገልጿል። ታላሚ የመማሪያ መጽሐፍ ከሰዋስው ይዘት ግልፅነት አንፃር ሁለቱም መጠነኛ ጉድለት የታየባቸው መሆኑ በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል። ከዚህ በመቀጠል ተተኳሪ መጽሐፍ ከሰዋስው ይዘት ግልፅነት አንፃር እንደ ሚከተለው ተፈትሸዋል።

4.2.1.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

የ7ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ከነድግግሞሻቸው በውስጡ ከያዛቸው 30 /ሠላሳ / የሰዋስው ይዘቶች በስድስት /6/ መልመጃዎች ላይ የግልጽነት ችግር ታይቷል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 20% ነው ። ይህ ደግሞ የሚያሳየው የመማሪያ መጽሐፍ ከግልጽት አኳያ ችግር እንዳለበት ያመለክታል ። ያሉትን የግልጽነት ችግር ለማሳያነት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 4. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የግልጽነት ችግሮች

| የክፍል ደረጃ | የሰዋስው ይዘት ርዕስ | የታየው የሰዋስው የችግር ዓይነት | ገጽ | ተግባር |
|---|---|---|---|---|
| 7ኛ | ተወሳከ ግስ ተውላጠ ስም እና መደብ | ግልጽነት | 86 | 10 |
| | ቃላት በተገቢ ቦታቸው መመደብ | ግልጽነት | 199 | 1 |
| | የተውሳከ ግስ መደብና አመልካች | ግልጽነት | 206 | 14 |
| | አዎንታዊ እና አሉታዊ | ግልጽነት | 216 | 15 |
| | መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር | ግልጽነት | 224 | 11 |

ከላይ በሰንጠረዥ 4. የተገለጹትን የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የግልጽነት ችግሮች ለአብነት ያህል የሚያሳይ ምሳሌዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ተግባር10

ተውሳከ ግስ፣ተውላጠ ስም እና መደብ

ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ወስጥ ያሉትን ቃላት በተገቢ ቦታቸው መደቡ።

| ዓረፍተ ነገር | በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ያለው የተውሳከ ግስ ዓይነት | | | በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ተውላጠ ስም | መደብ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የጊዜ | የቦታ | የሁኔታ | | |
| እሱ ትናንት እዚህ አልነበረም ። | | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እኔ ይህንን ጉዳይ በቀላሉ አላየውም ። | | | | | |
| አንቺ ወደ ወላጆችሽ ትሄጃለሽ ። | | | | | |

7ኛ ክፍል /2007፡ 86/

ከላይ የቀረበው አስረጅ በዐረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ የተለያዩ ቃላት ያላቸውን ሰዋስዋዊ ተገባር ተማሪዎች እንዲያውቁ ለማድረግ የታሰበ ይመስላል ። አቅራረቡ ግን ሰዋስዋዊ ግልፅነት የጎደለው ሆኖ ይታያል። ምክንያቱም ተውሳከ ግስ እና ተውላጠ ስም የራሳቸው የሆነ ተግባራት በዓረፍተ ነገር ውስጥ አላቸው። የቃላት ምደባ ተግባር ሲከውን ይህን መሰረት አድረጎ መሆን ነበረበት ። ተማሪዎች የቃላቱን ምንነት እንዲሁም ተግባራቸውን ለይተው ለመረዳት እንዲችሉ“የጊዜ ተውሳከ ግስ” ተግባሩ ድርጊት መቼ እንደተከናወነ መግለጽ ሲሆን “የቦታ ተውሳከ ግስ” በዓረፍተ ነገር ውስጥ ሚናው ድርጊት የተከናወነበትን ቦታን ግልጽ እንደሆነ በሚያሳይ መልኩ የተዋቀረ ሰዋስዋዊ ተግባር ያለው ግልጽ መልመጃ ሊሆን ይገባል። በጥቅሉ መማሪያ መጽሐፍ በተወሰነ መልኩ የግልፅነት ችግር እንዳለበት ማየት ተችሏዋል። እሱም የመልመጃውን አብይ ጉዳይ የሆነውን ሰዋስው ይዘትን ግልጽነት በጎደለው መልኩ ማቅረብ ነው።

ተግባር 1

የሚከተሉትን ሐረጋት በመነጠል እና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | በ-እስ -ተማማኝ | በእስተማማኝ |
| ለ | እንደ-ኣይ-በከል-ኡ | እንዳየበከሉ |
| ሐ | እንደ-ኣይ-ራብ-ኡ-ባቸው | እንዳይራቡባቸው |
| መ | ወደ -ምንመገብ-ሽው | ወደ ምንመገበው |

ከላይ የቀረበውን አስረጅ የመልመጃ ትዕዛዝ ፅንሰ ሃሳብ ስናይ ተማሪዎች በቀረቡት ሐረጋት ላይ የተቀጠሉ ቅጥያዎች አነባበብ ለይተው ወይም ተንትነው እንዲያነቡ የሚያዝ ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር ነው። ነገር ግን ያለምንም የሚያስረዳ ምሳሌ እንደቀረበ በታላሚው መጽሐፍ ላይ ለማየት ተችሉዋል ። ይሁን እንጂ

መጀመሪያ በነፃ ምዕላዱ ላይ ተቀጥለው ተነጣጥለው የሚነበቡትም ሆነ ተጣምረው የሚነበቡት ነጻ ምዕላድን እና ተቀጥያን ለመለየት የማያስችል ሆነው አልቀረቡም ። ይህ አቀራረብ ደግሞ ከሌሎች ምሳሌዎች አኳያ ሲታይ ተማሪዎች ያደናግራል ። ስለዚህ ግልፅነት ለመጠበቅ የግድ ሌሎች አብነቶች በቀረቡበት መልኩ ነጻ ምዕላድን እና ተቀጥያዎችን አጣምሮ የያዙ የተጣመሩ እና የተለያዩ ሐረጋትን ከነምሳሌያቸው መቅረብ ነበረባቸው። በመጀመሪያ በቀረበው አብነት"በ-አስ-ተማማኝ" በሚለው ሀረግ ላይ ተጣምሮም ሆነ ተነጣጥሎ ሲነበብ ምንም አይነት ልዩነት አለመኖሩን በፍተሻ ወቅት ለማየት ተችሉዋል።

#### 4.2.1.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ

የ8ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ በውስጡ ከነድግግሞሻቸው ከያዛቸው 30 የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ በ5 መልመጃዎች የትእዛዝ እና የምሳሌ አሰጣጥ ግልጽነት ችግር ታይቶባቸዋል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 16.7% ነው። እነዚህን ችግሮች በምሳሌ እንሚከተለው ቀርበዋል።

ተግባር 16

ስማዊ ሀረጎችን በመሙያነት በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን አሟልታቹ ጻፉ።

ምሳሌ፦ ጥያቄ፦ ካሳች-------- ነበረች።

መልስ፦ ካሳች ፈጣን ራጭ ነበረች።

ሀ. ሁለቱ ልጆች----- ናቸው።

ለ. አስቴር----------- ናት።

ሐ. አስቻለው---------ነው።

መ. አንተ------------- ነህ።

ሠ. አንቺ -------------- ነሽ።

ስምንተኛ ክፍል /2007፡91/

በአብነት የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ትዕዛዝ ግልፅነት የጎደለው ነው። ምክንያቱም ስማዊ ሀረግን ከመጠቀማቸው በፊት ወይንም ከገጽ 91 በፊት ምንም ዓይነት ስለስማዊ ሀረግ ጥቅምም ሆነ አመሰራረት የተማሩት የትምህርት ርዕስ አለመኖሩ የትምህርቱን ዓላማ ከባድ ከማድረጉም በሻገር በተማሪው ላይ ግርታን መፍጠሩ ዕሙን ነው። ይህ መሆኑ ደግሞ ሰዋስዋዊ መልመጃውን ግልፅነት የጎደለው ያደርገዋል። በሌላ

መልኩ ይህንን መልመጃ የሚሰሩ ተማሪዎች ከስማዊ ሀረግ ጥቅምና ምስረታ ጋር ምንም ዓይነት ትውውቅ ስለሌላቸውና ግለጽነት የጎደለው የሰዋስው ጥያቄዎችን በቀላሉ ሌሎች ቃላትን በክፍት ቦታው ላይ እንዲያስገቡ የሚጋብዝ ጥያቄ መሆናቸው የግልጽነት ችግር እንዲኖረው አድርጓል።

ለምሳሌ፡- አንቺ ጎበዝ ነሽ። /ስህተት/

አንተ ተማሪ ነህ።/ስህተት/

በማለት በመመለስ የትምህርቱን ዓላማ ሊስቱ ይችላሉ።

ስለዚህ እንዲህ አይነቱ የሰዋስው መልመጃ ትዕዛዝ ግልፅነትና ትክክለኛነት ስለ ሚጎድለው ተማሪዎችን ያደናግራል።

ተግባር 2

የሚለተሉትን ቃላትና ሀረጋት በፍጥነት ደጋግማችሁ አንብቡ።

ኮንቬንሽን

ሳይፈነጥዙ

በማይፈቅድላቸው

እንዲጫወቱ

የቤተሰቦቻቸውን

የትምህርታቸው

አጽድቋዋል

8ኛ ክፍል /2007፡144/

በእርግጥ የአማርኛ ቋንቋ እጅግ ብዙ ቃላትን ከተለያዩ ቋንቋዎች ቃላትን ተውሷል። ቢሆንም ግን በራሱ በቋንቋ ውስጥ በርከት ያሉ ለማንበብ አስቸጋሪ ቃላት አሉ። ነገር ግን በታላሚው መጽሐፍ ገጽ 144 ላይ የቀረቡት ቃላቶች ከባዕድ ቋንቋ ውስጥ የምታይባቸው ከመሆናቸውም በዘለለ ለማንበብ ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ሆነው አልተዘጋጁም። በተጨማሪም በመጽሐፉ ውስጥ በርካታ ከባዕድ ቋንቋ ውስጥ

የሚታይባቸው ከመሆናቸውም በዘለለ ለማንበብ ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ሆነው አልተዘጋጁም። በተጨማሪም በመጽሐፍ ውስጥ በርካታ ከባድ ቋንቋ ውስጥ የሚታይባቸው ቃላቶች ተሰድረው ይታያሉ።

ሠንጠረዥ 5. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በታላሚው ቋንቋ አቻ ፍቺ እያላቸው የተውሰ ቃላት

| የክፍል ደረጃ | የተውሰ ቃላት | ገጽ | ተግባር |
|---|---|---|---|
| 8ኛ | ፓርኩን | 136 | 1 |
| | ኮንቬንሽን | 144 | 2 |
| | ዲግሪ ሴንቲግሬድ | 193 | 2 |
| | ሜትሪዎሎጂ | 193 | 2 |
| | ግሪን ላንድ | 193 | 2 |

ለምሳሌ፡- ኮንቬንሽን

ኮንቬንሽን የሚለው ቃል የውሰት ከመሆኑ ባሻገር የተማሪውን የንባብ ክህሎት ያዳብራል ተብሎ አይገመትም። በተጨማሪም ቃሉን ሆነ ለመጠቀም አቻ ትርጉም ያለው ቃል መጠቀም ይሻላል። በሌላ መልኩ ለማንበብ የክፍል ደረጃውን ያላገናዘበ የቃላት ስደራው ተስተውለዋል።

እነዚህም፡-

ለምሳሌ፡-

ሳይፈነጥዙ

በማይፈቅድላቸው

እንዲጫወቱ

የቤተሰቦቻቸውን

ከትምህርታቸው

አጽድቋል

ከላይ የቀረቡት ቃላት ከተገቢነት አንፃር ሆነ ከግልጽነት ረገድ ደካማ መሆናቸው በሰነድ ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል። ይህም ሲባል የተቻለበት ምክንያት ምንም እንኳን ቃላቶች ረዣዥም ቢሆንም ተማሪዎቹ ካሉበት የክፍል ደረጃ ረገድ የቀረቡትን ቃላት ሊያነቡ ይገባል እንጂ እንደ ጅማሪ ተማሪ ፊደልን እየለቀሙ እንዲያነቡ የሚደረግ መልመጃዎች መቅረብ አልነበረበትም።

በጥቅሉ የተዘጋጁት ጥያቄዎች በዚህ የክፍል ደረጃ ከሚገኙ ተማሪዎች ዕድሜ እና የእውቀት ዳራ ታስቦ የቀረበ እንዳልሆነ የሚያሳው የክልሉ የስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ሲሆን በዚህ ፈተና ላይ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በታላሚው ክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች እንደሚያነቡ የሚሳዩ ጥያቄዎች ናቸው። በዚህ ምክንያት የመልመጃዎቹ አቀራረብ ደካማ ናቸው።

## 4.2.2. የመማሪያ መጽሐፍ ብቃት ከትክክለኛነት አንፃር

የሰዋስው ይዘት ትክክለኛነት ሲባል የተማሪውን ቋንቋ ስነ ልሳናዊ ባህሪ ወይም የተናጋሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታ ለሚመለከት ፅንስ ሃሳብ ነው። በአንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለትምህርትነት የሚካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ትክክለኛ መሆን ለመማር ማስተማሩ ሂደት ከፍተኛ አስተዋጾ አለው። በተቃራኒው ትክክለኛ ያልሆኑ ደግሞ ከፍተኛ ተጽኖ ያለው መሆኑን እሙን ነው።

በአጠቃላይ ትክክለኛነት በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከሚያቀርቡት መረጃ አንጻር ትክክለኛ መሆን እንደሚገባቸው በምዕራፍ ሁለት ለማየት ተችሏል። ታላሚ መጽሐፍ ከትክክለኛነት አንፃር ሲታይ በጥቂት የሰዋስው ይዘቶች ላይ የትክክለኛነት ችግር የታየባቸው መሆኑ በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል። ከዚህ በመቀጠል በተተኳሪ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ይዘቶችን ከትክክልኛነት አንፃር እንፈትሻለን።

#### 4.2.2.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

የ7ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ይዘቶች ትክክለኛነት መጓደል ታይቶበታል፡፡ መጻህፍት በውስጡ ከያዛቸው 30 የሰዋስው ይዘቶች በሦስቱ የቃላት እና የሀረግ ስያሜ ትክክለኛነት ችግር ታይቶባቸዋል ፡፡

ይህም በመቶኛ ሲሰላ 10% ነው፡፡ በሌላ መልኩ በአራት መልመጃዎች ደግሞ የሰዋስው ገለጻ ትክክለኛነት ችግር ታየቶባዋል፡፡ እነዚህ የሰዋስው መልመጃዎች ትክክለኛነት የሚታይባቸው ሽፋናቸውም በመቶኛ ሲሰላ 13.3%ነው፡፡

ሠንጠረዥ 6. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቃላት እና የሀረግ ስያሜ ትክክለኛነት ችግር እንዲሁም የሰዋስው ገለጻ ትክክልኛነት ችግር

| የክፍል ደረጃ | የቃላት እና የሀረግስያሜ ችግር | | | የሰዋስው ገለጸ ትክክለኘነት ችግር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ገጽ | ተግባር | የችግሮቹ አይነት | ገጽ | ተግባር | የችግሮቹ አይነት |
| 7ኛ | 78 | 1 | ቃላትን እንጂ ሀረጋትን አለመግለጽ | 133 | 13 | ሰዋስዋዊ ምሳሌ የሌለው መልመጃ |
| | 21 | 1 | ቃላትን እና ሀረጋትን ለየብቻ ማቅረብ ሲቻል በማደባለቅ የቀረበ መልመጃ | 180 | 14 | ሰዋስዋዊ ምሳሌ የሌለው መልመጃ |
| | 40 | 1 | ቃላትን ሀረጋትን ለየብቻ ማቅረብ ሲቻል በማደባለቅ የቀረበ መልመጃ | 198 | 12 | ሰዋስዋዊ ምሳሌ የሌለው መልመጃ |
| | | | | 62 | 13 | ግልጽ ያልሆነ ሰዋስዋዊ መልመጃ |

የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ቀደም ሲል እንደታዩት የመማሪያ መጽሐፍ ሁሉ የምሳሌ አሰጣጥ ትክክለኛነት ችግር ታይቶበታል፡፡

ለምሳሌ፡

ተግባር 13

የሚከተሉትን አያያዞች በመጠቀም ስድስት ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡

| |
|---|
| እና፣ ግን፣ እንጂ፣ ነገር ግን፣ ስለዚህ፣ ይሁን እንጂ |

7ኛ ክፍል /200፡133/

ከላይ ለአብነት የቀረበውን ጥያቄ ከትክክለኙነት አንጻር የመማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትክክለኛነት ችግር ታይቶበታል፡፡ይህንን የትክክለኛነት ችግርም እንደሚከተለው ተተንትኖዋል፡፡ይህ ጥያቄን እንደተመለከትነው ያለምንም አይነት ምሳሌ ለተማሪው ቀርበለታል፡፡

በመጀመሪያ ከመመሪያው ትክክለኛነት አንጻር ስንመለከተው ትዕዛዙ የሚለው የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም ስድስት ድርብ ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ፡ ነው እንጂ አያያዦቹ ለምን ተግባራት እንደሚለው/እንደሚጠቅሙ የተብራራበት ሁኔታ የለም፡፡ ስለዚህ መመሪያው የሚከተሉት አያያዦች በመጠቀም ድረብ አረፍተ ነገር መስርቱ፤ የሚል ቢሆን ትክክል ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ጥያቄው ለተማሪያ ለቀረበው ምንም አይነት የድርብ ዓረፍተ ነገር ምሳሌ በሌለበት መልኩ በመሆኑ በተማሪው ዘንድ መደናገርን ከመፍጠሩም በዘለለ የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከባድ ስለሚሆን የትክክለኛነቱን ተገቢነትም ጥያቄ ውስጥ ያስገባ መጽሐፍ መሆኑን መመዝገብ ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ምሳሌ፡-

ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላት ነጣጥላችሁ እና አጣምራችሁ አንብቡ፡፡

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | እንዲ-ያቀርቡ-ላቸው | እንዲያቀርቡላቸው |
| ለ | ተቃ-ውሞ-ኣቸውን | ተቃውማቸውን |
| ሐ | ዩናይ-ትድ-ኪንግ-ደም | ዩናይትድ ኪንግደም |
| መ | ኤዚ-ቢሽን | ኤግዚብሽን |
| ሠ | አ-ቋ-ቋመዋል | አቋቋመዋል |

7ኛ ክፍል /2007፡78/

ከላይ የቀረበውን የመልመጃ ትዕዛዝ ፅንስ ሃሳብ ስናይ ተማሪዎች በቀረቡት ቃላት ላይ የተቀጠሉ ቅጥያዎች አነባበብ ለይተው ወይም ተንትነው እንዲያነቡ የሚያዝ ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ለተማሪው በመልመጃነት የቀረቡት ጥያቄዎች ቃላትና ሃረጋትን አጣምሮ የያዙ ቢሆንም መመሪያው የሚለው

የሚከተሉትን ቃላት ነጣጥላችሁ እና አጣምራችሁ አንብቡ። ቃላትን እንጂ ሃረጋትን ባለመጠቀሱ የሰዋስው ይዘቱ ከትክክለኛነት አንፃር ትክክል አይደለም።

እንዲሁም ጥያቄው የቀረበው ያለምንም አስረጂ ምሳሌ አልቀረበም እንዲሁም መጀመሪያ በነፃ ምዕላዱ ላይ ተቀጥለው ተነጣጥለው የሚያነቡትም ሆነ ተጣምረው የሚያነቡት ነፃ ምዕላድን እና አቀራረብ ደግሞ ከሌሎች ምሳሌዎች አቀራረብ አኳያ ሲታይ ተማሪዎችን ያደናግራል። ምክንያቱም ቃሉ የተውሶ ስለሆነ ተማሪዎች የቃሉን ስረው ቃል ካላወቁት በአማርኛ የሰዋስው ህግጋት ተመርጠው ሊፈፅሙ ይችላሉ።

### 4.2.2.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

መማሪያ መጽሐፍ ከትክክለኛነት አንፃር እስካሁን ካየናቸው የመማሪያ መጽሐፍ የተለዩ አይደሉም። የ8ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ከነድግግሞሹ ከያዛቸው 30 የሰዋስው ይዘቶች የቃል እና የሐረግ ሰዋስዋዊ ስያሜ ችግር በ7 መልመጃዎች ላይ ታይቷል።

እንዲሁም ሰዋስው ትክክለኛነት ችግር ደግሞ በ4 የሰዋስው ይዘቶች ላይ ታይቷል። በድምሩ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ 11 የሰዋስው መልመጃዎች የግልጽነት ችግር ሲኖርባቸው ከጠቅላላው 36.6% መሆኑን በሰነድ ፍተሻ ተረጋግጧል።

ተግባር **16**

በምሳሌው መሰረት ተውሳከ ግሶች መጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ

- ሰሚራ - ሁልጊዜ - ትጠጣለች
- ቾሩ - አንድ ጊዜ -ለስላሳ - ይጠጣል
- ከድር - አልፎ አልፎ - ይጠጣሉ
- ቾርነት - ቶሎ
  -በፍጥነት
  - በቀስታ

<u>ምሳሌ</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰሚራ | ሁል ጊዜ | ለስላሳ | ትጠጣለች። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቸሩ | አንዳንድ ጊዜ | ለስላሳ | ይጠጣል። |
| ከድርና ቸርነት | አልፎ አልፎ | ለስላሳ | ይጠጣሉ። |

8ኛ ክፍል /2007፡152/

ከላይ በአስረጂነት የቀረበው መልመጃ ትዕዛዝ በምሳሌው መሰረት ተውሳከ ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ ይበል እንጂ ተማሪዎች እንዲለማመዱባቸው የቀረቡት መዋቅሮች ስም፣ግስ፣ተውሳከ ግስን አንድ ላይ አጣምሮ የያዘ መመሪያ በመሆኑ የመመሪያ ግልጽነት ችግር እንዲጎላ አይነተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

በተጨማሪም የመመሪያው ጥቅል መሆን መልመጃውን ተማሪዎች እንዲሰሩት የማይጋብዝ ከመሆኑም በላይ እንዲናገሩ የሚያደርግ ትዕዛዝ በመሆኑ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ሊቀርብ የሚገባ አብይ ጉዳዩ ነው።

ስለዚህ ተውሳከ ግሶችን ለብቻ በመነጠል እና ትኩረት በማድረግ ግልጽ በሆነ መልኩ ከቀረበው ምሳሌ ይልቅ ለተማሪው ግልጽ እና ትክክለኛ መመሪያ ስለሚሆን ሊስተካከል የሚገባ የትክክለኛነት ግድፈት ነው። በሌላ መልኩ የመማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ገጽታ ትክክለኛነት ችግር ይታይበታል።

ለምሳሌ;

በሚከተሉት ዋና ቃላት ላይ የመነሻና የመድረሻ ቅጥያዎች በመጨመር የተለየ ፍች ያላቸውን ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ፡- ወረደ፣ ማውረድ፣ ውርደት፣ አዋረደ፣ ውርጃ፣ ውርድ

ሀ. መጣ ለ. ገነባ ሐ.ኖረ መ.ፈለገ

ሠ.ለመደ ረ. በቃ ሰ. ፈጠረ ሸ.ቀጠለ

8ኛ ክፍል/2007/

ከላይ በቀረበው አስረጂ የመልመጃ ትዕዛዝ ላይ ዋና ቃል የሚል መዋቅር ቀርቧል። ይሁን እንጂ የቃላት አመሰራረት ሂደትን አምድ እና ስር የሚሉ ቃላት ሰዋስዋዊ ብያኔዎች እንጂ ''ዋና ቃል'' የሚል የለም። ስለሆነም ዋና ቃል የሚለው አንድ አምድ የሚለውን እሳቤ የያዘ ይመስላል። ምክንያቱም ማንኛውም እስር ምዕላድን ሊያስቀጥል የሚችል ነፃ ወይም እስር አሀድ አምድ ስለሚባል ቢስተካከል ተመራጭ ነው።

ከቀረበው ገለፃ አንፃር በምሳሌነት የቀረበው ''ወረደ'' የሚለው መዋቅር አምድ አይደለም። ምክንያቱም ''ወረደ'' የሚለው ቃል /ወረድ-/ከሚለው እስር አምድ እና ጾታ፣መደብ፣ቁጥር፣ ባለቤት አመልካች ከሆነው ''ኧ''የተመሰረተ ነው። ስለሆነም /ወረድ-/የሚለው መዋቅር ማንኛውም ቅጥያ ማስቀጠል የሚቻል አምድ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ዋና ቃል በተባለው''ወረደ''ላይ የመነሻና የመድረሻ ቅጥያዎችን በመቀጠል ቃላት መስርቱ የሚለው ትዕዛዝ የተመሰረቱት ምስረታ ቃላት የሚጣጣሙ አጥደሉም። ምክንያቱም የተመሰረቱት ቃላት ''ወረደ'' እርሱ ቅርጹን በመቀያየር ውርደት፣ ውርጃ፣ውርዴ፣የሚሉትን ቃላት መስርቷል። የእነዚህ ቃላት አምድ ደግሞ (ውርድ-) ነው።

የወሰዳቸው ቅጥያዎችም ''ኧት'' እና ''ኤ'' ናቸው። ስለዚህ በመድረሻ ቅጥያነት ት፣ጃ፣ዴ፣ ተብሎ መቅረባቸው የይዘቱን ትክክለኛነት አጓድሎታል። በአጠቃላይ ተተኳሪ የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ የቃላት እና የሀረጋት ሰዋስዋዊ ስያሜ በትክክለኛ ቦታቸው ያለመጠቀም ችግር ጎልቶ የታየባቸው መሆኑን በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል።

ከዚህ በተጨማሪ ይህ ችግር በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ላይ መከሰቱ በየደረጀው የሚማሩ ተማሪዎች ከክፍል ወደ ክፍል ሲዘዋወሩም ደጋግመው ስለሚያዩ የቃል እና የሀረግ ምንነትን በግልጽ ለመረዳት ይሳናቸዋል። ይህም የቋንቋ ትምህርቱን ግብ የሚፈታተን ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል። ይህ ደግሞ ተማሪዎች በትህርትነት የቀረበውን የሰዋስው ይዘት በተገቢው መልኩ ለመረዳት ያስቸግራቸዋል።

### 4.2.3. የመማሪያ መጽሐፍ ከተመጣጣኝነት አንፃር

በአንድ የቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የስነ-ድምፅ፣ የስነ-ምዕላድ፣ የስነ-አገባብ፣ እና የስነ-ፍቺ የሰዋስው ይዘት ክፍሎች ፍትሃዊ በሆነ አኳኋን ተውጣጥተው መቅረብ እንዳለባቸው በምዕርፍ ሁለት ውስጥ ተገልጧል። ይህም  ሲባል ግን በአንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም የሰዋስው ይዘቶች በእኩል ደረጃ ተካተው መገኘት አለባቸው በማለት አይደለም። እንደ ተማሪዎች አይነት ወዘተ እንደ አስፈለጊነቱ ለተወሰኑት የሰዋስው ክፍሎች የበለጠ ትኩርት ሊሰጥ ይችላል። ሆኖም ግን በአንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ይዘት ክፍሎች እጅግ

ባልሰፋ መልኩ ሁሉንም በመዳሰስ መቅረብ አለባቸው። አቀራረባቸውም በልዩ ልዩ የመልመጃ የአቀራረብ ስልቶች መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ከዚህ የንድፈ ሃሳብ አንፃር በጥናቱ ታላሚ የሆኑትን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ገፅታ ይዳስሳል።

### 4.2.3.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በታላሚ መጽሐፍ ውስጥ ስነ-ምዕላድን እና ስነ-አገባብን በተመለከተ የጎላ ችግር አል ታየበትም። ይህም ሲባል የመማሪያ መጽሐፍ ከስነ-ምዕላድ እና ከስነ-አገባብን ገረድ ትኩረት ተሰቶበታል ለማለት ይቻላል።

ይህም የሚያሳየው የመማሪያ መጽሐፍ ጠንካራ ሆኖ የተገኘው ከስነ-ድምፅ ሽፋን አንጻር መሆኑን ነው።

ሠንጠረዥ 7. በ7ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተመጣጣኝነት ገጽታ

| ስነ- ድምፅ | | ስነ-ምዕላድ | | ስነ-አገባብ | | ስነ- ፍች | | የሰዋስው ይዘቶች ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | 30 |
| 2 | 6.7% | 10 | 33.3% | 11 | 36.7% | 7 | 23.3 | |

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከሰዋስው የትምህርት ይዘቶች ጋር በመያያዝ የተዘጋጁ መልመጃዎች ዝቅተኛ ሽፋን የያዘው ስነ ድምፅ ነው። ሽፋኑ በመቶኛ ሲሳላ 6.7% ብቻ ነው። በሰዋስው ይዘት ውስጥ ስነ ፍቺን አስመልክቶ የቀረቡት መልመጃዎችን ሽፋን በመቶኛ ስንመለከተው 23.3% ነው።

በዚህም መስረት ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት ስነ-ምዕላድ እና ስነ- አገባብ ናቸው። ሽፋናቸውም እንደቅደም ተከተላቸው 33.3% እና 36.7% ሆኖ ተገኝቷል።

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች የመልመጃ አቀራረብ፡- በምሳሌ በተደገፈ ገለፃ፣ በአዛምድ፣ በምርጫ፣ የተዘበራረቁ ቃላትን በማስተካከል፣ ቃላት እና ሀረጋትን በመመስረት ለቃላትና ለሀረጋት ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍች መስጠትም አሉታዊ አረፍተ ነገሮችን ወደ አዎንታዊ መቀየርን የመሳሰሉ በርካታ መልመጃዎች ናቸው።

ይህም የሚያመለክተው በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው መልመጃዎች የጥያቄ አወጣጥ ሁኔታበልዩ ልዩ ስልት መቅረባቸው ነው።

#### 4.2.3.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ

የ8ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ስነ- ምዕላድን በተመለከተ በርካታ ቁጥር የያዘ ሲሆን ስነ-ፍቺ እና ስነ-አገባብን በተመለከተ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ከስነ-ድምፅ በተሻለ ሁኔታ ሽፋን አላቸው። ይህም የሚያሳየው የመማሪያ መጽሐፍ ለስነ-ድምፅ ትኩረት አልሰጠም።

ሠንጠረዥ 8. በ8ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተመጣጣኝነት ገጽታ

| ስነ- ድምፅ | | ስነ-ምዕላድ | | ስነ-አገባብ | | ስነ- ፍቾ | | የሰዋስው ይዘቶች ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | |
| 2 | 6.7% | 11 | 36.6% | 9 | 30 | 8 | 26.7% | 30 |

የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች እስከ አሁን እንዳየናቸው ከአራቱ የሰዋስው የይዘት ክፍሎች የተወጣጡ ናቸው። የስርጭት መጠናቸውን በተመለከተም ስነ-ፍች 26.7%፣ ስነ- አገባብ 30% ፣ስነ- ምዕላድ 36.6% እና ስነ- ድምፅ 6.7% የሽፋን ድርሻ ይዘዋል። የመልመጃዎቹ አቀራረብም በሌሎች የመማሪያ መጽሐፍ ከጠቀስናቸው ልዩ አቀራረብ ስልቶች ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

### 4.2.4. የመማሪያ መጽሐፍ ከተገቢነት አንጻር

በአንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተገቢነት አላቸው የሚያገኘው በመርሃ ትምህርቱ ከተነደፈው የቋንቋ ትምህርት አላማ ጋር ሲጣጣም ከተማሪዎች ዳራዊ ዕውቀት፣ ዕድሜ፣ የመስራት እና የማገናዘብ ችሎታ ጋር የተገናዘቡ መሆን አለባቸው። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑትን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምን አይነት ገፅታ እንዳላቸው እያንዳንዳቸው በቅደም ተከተል እናያለን ።

#### 4.2.4.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ

የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ ያልተጠቀሱ የስነ- ምዕላድ፣ የስነ- አገባብ ፣ የስነ-ፍቺ እና የስነ- ድምፅን ንዑስ ይዘቶች ተጠቃለው በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ እንዲሁም በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡

በመርሃ- ትምህርቱ ተጠቅሰው በመማሪያ መጽሐፍ ያልተጠቀሱ ወይም በመማሪያ መጽሐፍ ተጠቅሰው በመርሃ ትምህርቱ ያልተካተቱ ምንም አይነት ይዘቶችን በሰነድ ፍተሻው አልታዩም፡፡ ስለዚህ መርሃ- ትምህርቱ እና የተማሪው መጽሐፍ የተጣጣመ ነው፡፡

#### 4.2.4.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ልዩ ልዩ የተገቢነት ጉድለት ታይቶበታል፡፡ ተገቢነትን በተመለከተ በመርሃ ትምህርቱ ተጠቅሰው በመማሪያ መጽሐፍ ያልተጠቀሱ እንዲሁም በመማሪያ መጽሐፍ ተጠቅሰው በመርሃ ትምህርቱ ያልተጠቀሱ የሰዋስው ይዘቶች አለመኖራቸውን በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል፡፡ ይህ ደግሞ የመመሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ይዘት ተገቢነት ያሳያል፡፡

## 4.3. የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀት

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ሲባል በ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተከታትለው እና ተለጣጥቀው በምን መልኩ እንዴት ተደጋግመው ተደራጅተው መቀመጥ እንዳለባቸው የሚገልጽ ፅንሰ ሀሳብ መሆኑን በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡

### 4.3.1. ከተከታታይነት አንጻር

ተከታታይነት ለአንድ የክፍል ደረጃ ተወስኖ በተዘጋጀ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተደራጁ ይዘቶች ድግግሞሽን የሚመለከት ፅንሰ ሀሳብ የያዘ መሆኑን በምዕራፍ ሁለት ተገልጻል፡፡

ይህም ተማሪዎች በትምህርትነት የቀረቡት ይዘቶችን በአግባቡ እንዲረዷቸው እና በሂደት ስለቀረቡት ይዘቶች ያላቸው ግንዛቤ እያደገ እንዲሄድ ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ታላሚ የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተካተው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን ችግር ያለባቸው ወይም

የሌለባቸው መሆኑን ቀጥሎ በሚቀርበው ሠንጠረዥ ተተኳሪ መጽሐፍ ምን አይነት ገፅታ እንዳላቸው እናያለን፡፡

### 4.3.1.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በውስጡ 30 የሰዋስው ይዘቶችን የያዘ ሲሆን አብዛኞቹ ይዘቶች ተደጋግመው ቀረቡ እንጂ ተከታታይነታቸውን በጠበቀ መልኩ ተደራጅተው የቀረቡ አይደሉም፡፡

በጥቅሉ ዘጠን የሰዋስው ይዘቶች ተከታታይነት አይታይባቸውም፡፡ ይህም በመቶኛ ሲታሰብ 30 በመቶ ሽፋን ይዟል፡፡

ሠንጠረዝ 9. 7ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን

| የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ታላሚ የ7ኛ ክፍል የተማሪው መጽሐፍ | በመቶኛ |
|---|---|---|
| ስነ ድምፅ፡- በቃላት ውስጥ የድምፅ መጥበቅና መላላት | 0 | 0 |
| በድምፅ ክትትሎሽ ሳቢያ የሚከሰት የድምፅ መዋጥ | 1 | 3.3 |
| በቃል ውስጥ ያሉ ሆሄያትን ቦታ በመቀያየር የተለያዩ ቃላት መመስረት | 0 | 0 |
| ስነ ምዕላድ ፡- ቅጥያዎችን መለየት | 2 | 6.7 |
| ቅጥያዎችን በዋና ቃል ላይ በመጨመር ቃላት መመስረት | 2 | 6.7 |
| ማሰሪያ አንቀፅ ከሆኑ ቃላት የስምና የግስ ገላጭ መመስረት | 2 | 6.7 |
| ድርብ ቃላት መመስረት | 1 | 3.3 |
| ምሀጻረ ቃላትን መመስረት | 1 | 3.3 |
| ስነ አገባብ፡- ሀረግ ምስረት | 2 | 6.7 |
| ዐረፍተ ነገር ምስረታ | 3 | 10 |
| የዐረፍተ ነገር ባለቤት እና ማሰሪያ አንቀጽ በፆታ እና በቁጥር ማስማማት | 2 | 6.7 |
| ቃልን ፣ሀረግን እና ዐረፍተ ነገርን መለየት | 3 | 10 |
| የስም ገላጩን መለየት | 0 | 0 |
| የተዘበራረቁ ቃላትን ቅደም ተከተል በማሲያዝ የተስተካከለ ዐረፍተ ነገር መመስረት | 2 | 6.7 |
| የሰዋስው ግድፈት ያለባቸውን ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ መጻፍ | 1 | 3.3 |
| የተጓደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በተገቢ ቃላት ማሟላት | 0 | 0 |
| የዐረፍተ ነገር ስልቶች | 1 | 3.3 |

| | | |
|---|---|---|
| በዐረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ሙያ መግለጽ | 0 | 0 |
| ግላጮችን በመጨመር አረፍተ ነገርን ማጎልበት | 0 | 0 |
| የዐረፍተ ነገር ዓይነቶችን መግለጽ | 1 | 3.3 |
| ስነ ፍች፡- የቃላት ዕማሪያዊ /መዝገበ/ ቃላዊ ፍች | 0 | 0 |
| የቃላት አውዳዊ ፍች | 0 | 0 |
| የቃላት ተመሳሳይ ፍች | 1 | 3.3 |
| በፍች የተለየውን ቃል መምረጥ | 1 | 3.3 |
| የአያያዥ የተለየውን ቃል መምረጥ | 0 | 0 |
| የአያየዥ ቃላት አጠቃቀም | 3 | 10 |
| የሀረግ አውዳዊ ፍቺ | 0 | 0 |
| የዐረፍተ ነገር ተመሳሳይ ፍች | 1 | 3.3 |
| ድምር | 30 | 100 |

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች የዐረፍተ ነገር ምስረታ 10 በመቶ የቃላት ተመሳሳይ ፍች 3.3%፣ የቃላት ተቃራኒ ፍች 3.3%፣ የቃላት አውዳዊ ፍች የለም ማሰሪያ አንቀፅ ከሆኑ ቃላት የስም እና የግስ ገላጭ መመስረት 6.7%፣ ቅጥያዎችን በዋና ቃል ላይ በመጨመር ቃላት መመስረት 6.7%፣ የተጓደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በተገቢ ቃላት መሙላት የለም የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም 10% እና የቃላት እማሬያዊ ፍች የለም በቃል ውስጥ የድምፅ መጥበቅ እና መላላት የለም፤ በቃል ውስጥ ያሉ ሆሄያትን ቦታ በመቀያየር የተለያዩ ቃላት መመስረት የለም፤ የስም ገላጭን መለየት የለም፤ የሰዋስው ግድፈት ያለባቸውን ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ መጻፍ 3.3%፣ ገላጮችን በመጨመር ዐረፍተ ነገር ማስፋፋት የለም፡፡

በተመሳሳይ ድምፅ ክትትሎሽ ሳቢያ የሚከሰት የድምፅ መዋጥ 3.3 %፣ ቅጥያዎችን መለየት 6.7%፣ ምህፃረ ቃላትን መመስረት 3.3%፣ የተዘበራረቁ ቃላት ቅደም ተከተል በማስያዝ የተስተካከለ ዐረፍተ ነገር መመስረት 6.7%፣ በዐረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ሙያ መለየት የለም፤ በፍች የተለየውን ቃል መምረጥ የለም እና የሀረግ ፍች አልታየም፡፡

ይህም ከላይ እንደታዩት መጽሐፍ ሁሉ ከፍተኛ ሽፋን በያዘው የሰዋስው ይዘት እና ዝቅተኛ ሽፋን በያዘው መካከል ያለው ልዩነት ስላሳየ መጽሐፉ አደረጃጀት ችግር ያለበት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ያም ሆነ ግን በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ አብዛኞቹ የሰዋስው ይዘቶች አለመመጣጠን እንጂ ተከታታይነታቸውን ጠብቀው የተገኙ ናቸው ማለት ይቻላል። ለማስረጃነት ያህል ባልተመጣጠነ መልኩ በተደጋጋሚነት የቀረበ መልመጃን እንመለከታለን።

ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት በመነጣጠል እና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | በ-ኢትዮጵያ-ም | በኢትዮጵያም |
| ለ | ከ-ሚተላለፍ-ብ-ኣቸው | ከሚተላለፍባቸው |
| ሐ | ሊጠቀም-ኡ-ኣቸው | ሊጠቀማቸው |
| መ | በ-ምታ-ባ-ብ-አት-ም | በምንታጣበትም |
| ሠ | የሚታወቅ-አው-ን | የሚታወቀውን |
| ረ | እየ-አንዳንድ-ኣችን | እያንዳዳችን |
| ሰ | የሚችል-ኡ-ኣቸውን | የሚችላቸውን |

7ኛ ክፍል /2007፡40/

ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላት በመነጣጠል እና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበቡ |
|---|---|---|
| ሀ | አጎል- ብተን-ኣል | አጎልብተናል |
| ለ | ተ-ወካይ-ነት-ህ | ተወካይነትህ |
| ሐ | ሐዘን-ተኛ-ው-ን | ሐዘንተኛውን |
| መ | ግንኙ-ነት-ኣችን | ግንኙነታችን |
| ሠ | ደንብ-ኣችን | ደንባችን |
| ረ | አቀርብ-ልሽ-አለሁ | አቀርብልሻለሁ |
| ሰ | አረጋዊ-ያን-ና | አረጋዊያንና |

7ኛ ክፍል /2007፡128/

ከላይ ለአስረጅነት የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ተማሪዎች ቃላት በመነጣጠል እና በማጣመር እናዲያነቡ ይጋብዛል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ ለአብነት የቀረቡት ሁለት ማስረጃዎችን እንደተመለከትነው ያለ ምንም የመመሪያም ሆነ የመልመጃ ልዩነት በታላሚው መማሪያ መጽሐፍ ላይ ተደጋግመው በገጽ 40 ላይ እና በገጽ 128 ከላይ የተገለጹትን ተመሳሳይ መልመጃዎች ይታያሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው በተደጋጋሚ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች ተከታታይነታቸውን ጠብቀው መገኘታቸውን ነው፡፡

## 4.3.1.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ በውስጡ ከያዛቸው 30 የሰዋስው ይዘቶች በውስጥ አካቶአል፡፡ ከነዚህ የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ በ10/አስሩ/ ድግግሞሽ ታይቶባቸዋል፡፡ ይህም ከጠቅላላው ሽፋናቸው 33.3% እንደሆነ የሰነድ ፍተሻው አሳይቶዋል፡፡

ስለዚህ ከገለፃው እንምንረዳው ቀላል የማይባሉ የሰዋስው ይዘቶች ድግግሞሽ እንደታየባቸው ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች አብዛኞቹ ተከታታይነታቸውን የጠበቁ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 10. 8ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን፡፡

| የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ታላሚ የ8ኛ ክፍል የተማሪው መጽሐፍ | በመቶኛ |
|---|---|---|
| ስነ ድምፅ፡- በቃላት ውስጥ የድምፅ መጥበቅና መላላት | 0 | 0 |
| በድምፅ ክትትሎሽ ሳቢያ የሚከሰት የድምፅ መዋጥ | 1 | 3.3 |
| ስነ ምዕላድ ፡- ቅጥያዎችን መለየት | 2 | 6.7 |
| ቅጥያዎችን በዋና ቃል ላይ በመጨመር ቃላት መመስረት | 2 | 6.7 |
| የተጓደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በተገቢ ቃላት ማሟላት | 2 | 6.7 |
| የአያየዥ ቃላት አጠቃቀም | 3 | 10 |
| የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም | 1 | 3.3 |
| ስነ አገባብ፡- ሀረግ ምስረት | 1 | 3.3 |

| | | |
|---|---|---|
| ዐረፍተ ነገር ምስረታ | 1 | 3.3 |
| በቃላት ላይ ባሉ አፀፋዎች አማካይነት መደብን መለየት | 1 | 3.3 |
| ተፈጥሯዊ ፆታ መለየት | 1 | 3.3 |
| የዐረፍተ ነገር ባለቤት እና ማሰሪያ አንቀጽ በፆታ እና በቁጥር ማስማማት | 2 | 6.7 |
| ቃልን ፣ሀረግን እና ዐረፍተ ነገርን መለየት | 2 | 6.7 |
| የስም ገላጩን መለየት | 0 | 0 |
| የተዘበራረቁ ቃላትን ቅደም ተከተል በማስያዝ የተስካከለ ዐረፍተ ነገር መመስረት | 2 | 6.7 |
| የሰዋስው ግድፈት ያለባቸውን ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ መጻፍ | 2 | 6.7 |
| ስነ ፍቺ፡- የቃላት ዕማሪያዊ /መዝገበ/ ቃላዊ ፍች | 0 | 0 |
| የቃላት አውዳዊ ፍች / | 1 | 3.3 |
| የቃላት ተመሳሳይ ፍች | 2 | 6.7 |
| የቃላት ተቃራኒ ፍች | 1 | 3.3 |
| የሀረግ ፍቺ | 0 | 0 |
| የሀረግ አውዳዊ ፍቺ | 0 | 0 |
| የሀረግ ተቃራኒ ፍቺ | 1 | 3.3 |
| የዐረፍተ ነገር ተመሳሳይ ፍች | 2 | 6.7 |
| ድምር | 30 | 100 |

የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች መጠንን ከዚህ በመቀጠል በቅደም ተከተል እንመለከታለን። ይኸውም የዐረፍተ ነገር ምስረታ 3.3%፣ የቃላት አውዳዊ ፍች 3.3%፣ የቃላት ተቃራኒ ፍች 3.3%፣ የቃላት ተመሳሳይ ፍች 6.7%፣ የተጓደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በተገቢው ቃላት ማሟላት 6.7%፣ በቃላት ወስጥ ያሉ ድምጾች መጥበቅና መላላት የለም፤የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም 10%፣ የሀረጋት ፍቺ የለም፤ የሰዋስው ግድፈት ያለባቸውን ዓረፍተ ነገሮች አስተካክሎ መጻፍ 6.7%፣ የአረፍተ ነገር አይነቶችን መግለጽ 6.7%፣ ቃላት ሀረጋትና አረፍተ ነገር መለየት 6.7%፣ የአረፍተ ነገር ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ በጾታ እና በቁጥር መስማማት 6.7%፣ የቃላት እማሪያዊ ፍቺ የለም፤ ቅጥያዎችን መለየት 6.7%፣ ቅጥያዎችን በዋና ቃል ላይ በመጨመር ቃላት መመስረት 6.7%፣ ምህፃረ ቃላት መመስረት የለም፤ የተዘበራረቁ ቃላትን ቅደም ተከተል በማስያዝ የተስተካከለ ዐረፍተ ነገር መመስረት 6.7%፣ በተመሳሳይ ድምጽ ክትትሎሽ ሳቢያ የሚከሰት ድምጽ መዋጥ 3.3%፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም 3.3%፣ ተፈየጥሮአዊ ጾታን መለየት 3.3%፣ በቃላት ባሉ አጸፋዎች አማካኝነት መደብን መለየት 3.3%፣ ማሰሪያ አንቀጽ ከሆኑ ቃላት የስምና የግስ ገላጭ መመስረት የለም፤በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ያሉ ቃላት የስምና የግስ ገላጭ መመስረት የለም፤ድርብ ቃላት መመስረት የለም፤ በአረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ቃላትን ቦታ በመቀያየር የሚያመጣውን የፍቺ የለውጥ ማየት የለም፤ ሀረግ

ምስረታ 3.3%፣ ገላጨችን በመጨመር ዓረፍተ ነገር ማጎልበት የለም፤የሀረግ ተቃራኒ ፍቺ 3.3%፣ እና የአረፍተ ነገር ተመሳሳይ ፍቺ 6.7% ሽፋን ይዘዋል፡፡

ይህም መጽሐፍ በውስጡ ያያዛቸው የሰዋሰው ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን እጅግ የተራራቀ መሆኑን ያሳያል፡፡

### 4.3.2. የመማሪያ መጽሐፍ ከተለጣጣቂነት አንፃር

ተለጣታቂነት ከተከታይነት ጋር የሚዛመድ ፅንስ ሃሳብ ያለው ሆኖ ተደጋግመው የሚቀርቡ የሰዋስው ይዘቶች በየደረጃው ስፋትና ጥልቀት እያገኙ መሄድ እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ፅንስ ሃሳብ መሆኑን ተገልጧል፡፡ ከዚህ አንፃር በታላሚ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ይዘቶች የተለጣጣቂነት ጉድለት ያለባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ይህንንም ቀጥለው በቀረቡ በሰባተኛ ክፍል እንዲሁም በስምንተኛ ክፍል በተመሳሳይ መልኩ የቀረቡትን መልመጃዎች በምሳሌነት ቀርበዋል፡፡

ሰባተኛ ክፍል

ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት በመነጣጠል እና በማጣመር አንብቡ፡፡

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | በ-ኢትዮጵያ-ም | በኢትዮጵያም |
| ለ | ከ-ሚተላለፍብ-ኣቸው | ከሚተላለፍባው |
| ሐ | ሊጠቀም-ኡ-ኣቸው | ሊጠቀማቸው |
| መ | በ-ምታ-ባ-ብ-አት-ም | በምንታጣበትም |
| ሠ | የሚታወቅ-አው-ን | የሚታወቀውን |
| ረ | እየ-አንዳንድ-ኣችን | እያንዳንዳችን |
| ሰ | የሚችል -አ-ኣቸው-ን | የሚችላቸውን |

7ኛ ክፍል /2007፡40/

ስምንተኛ ክፍል

ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት በመነጣጠል እና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ተጠቃሚ-ነት | ተጠቃሚነት |
| ለ | ግብአት-ኦች-ኣችን | ግብአቶቻችን |
| ሐ | መሰረት -ኣ-ልማት -ኦች | መሰረተ ልማቶች |
| መ | ውጤት -ኣማ-ነት | ውጤታማነት |
| ሠ | ለማድ-ኦች-ኣችን | ልማዶቻችን |
| ረ | መስራት -ኣቸው-ን | መሰረታቸውን |
| ሰ | አካባቢ-ያቸው-ን | አካባቢያቸውን |
| ሸ | ማህበር -አ-ሰብ-ኣዊ-ነት | ማህበረሰባዊነት |

8ኛ ክፍል /2007፡17/

ከዚህ በላይ በታላሚዎቹ ክፍል መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ሁለቱም ተመሳሳይ መልኩ ተደራጅተው የቀረቡ ናቸው። ይህም ቃላትን ወይም ሀረጋትን ነጣጥለው እና አጣምረው እዲያነቡ የሚያለማምዱ ፍጹም ተመሳሳይነት ያላቸው በታላሚዎቹ የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚገኙ መልመጃዎች ናቸው ።

ይህም የሚያሳየው በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ይዘቶች ስፋና ጥልቀት ሳይጨምሩ በተመሳሳይ የአደረጃጀት ሂደት በሰባተኛም እንዲሁም በስምንተኛም እንዲሁም በስምንተኛ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ መገኘታቸውን ነው። በዚህም ምክንያት የሰባተኛ  ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስብስብነት ያለው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

በአጠቃላይ በስምንተኛ ክፍል የተጠቀሰው በሰባተኛ ክፍል ከተጠቀሰው የሰዋስው ይዘት ልዩነት በሌለው መልኩ እንዲሁም ስፋት እና ጥልቀትን አልባ ሆነው ተደራጅተው መቅረባቸውን ነው። ከክብደት አንፃርም ሲመዘኑ ልዩነት የላቸውም። ስለዚህ ከላይ ባየናቸው መጽሐፍ ውስጥ የተለጣጣቂነት ችግር መኖሩን ያሳየናል።

## 4.4. የመማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው አቀራረብ ገፅታ

የዚህ ጥናት አጥኚ ሌላው ዋነኛው የጥናቱ ትኩረት የሆነው በምዕራፍ አንድ አላማ ስር እንደተጠቆመው የታላሚ የመማሪያ መጽሐፍ የሰዋሰው አቀራረብ ገጽታን መፈተሽ በመሆኑ ቀጥለው ባሉት ንዑስ ርዕሶች ስር እንደሚከተለው ተብራርተው ቀርበዋል።

### 4.4.1. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ

ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ይዘት አቀራረብ መርህ የቋንቋ ህግ የሚያስረዳ ትንታኔ ለተማሪዎች በማቅረብ በቀረበው ትንታኔ መሰረት የተሰጣቸው ልዩ ልዩ መልመጃዎች በመስራት ወደ ህግጋቱ እንደሚደርሱ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል።

ከዚያም የተለያዩ ጥልቅ ምሳሌዎች ይሰጡ እና ወደ ዝርዝር ተግባር (ልምምድ) ይገባሉ። በዚህም መሰረት ተማሪዎች የተሰጣቸውን ሰዋስዋዊ ፅንስ ሃሳቦች እና ምሳሌዎች ከተረዱ በኋላ ቀጥለው የሚቀርቡላቸው የተግባር መልመጃዎች በመስራት በሂደት ትክክለኛን የቋንቋን ስርዓት አጠቃቀም ይገነዘባሉ።

ታላሚ መጽሐፍ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ይዘት አቀራረብ ስልትን በተመለከተ ጉድለት አለባቸው። በዚህ መሰረት ተተኳሪ መጽሐፍ በክፍል ደረጃቸው ቅደም ተከተል መሰረት በውስጣቸው ያካተታቸው የሰዋስው ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ገጽታ ቀጥለው ይፈተሻሉ።

#### 4.4.1.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በሰባተኛ ክፍል ተማሪው በውስጡ ከያዛቸው የሰዋስው ይዘቶች (ገጽ 62 እና 95) የሚገኙ ሁለት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ብቻ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ይዘት አቀራረብ መርህን ተከትለው ቀርበዋል።

ይህም በመቶኛ ሲሰላ 6.7% ከላይ የተገለጹት የሰዋስው ይዘቶች መልመጃ አቀራረብ በመጀመሪያ ስለያዙት ሰዋስዋዊ ይዘት ምንም ማብራሪያ ወይም ገለፃ ሰጥተዋል።

በመቀጠል ለገለፃው አስረጂ የሆኑ አብነቶች ቀርበዋል። በመጨረሻም ለተማሪዎች መለማመጃ የሚሆን ተግባራት ተሰጥተዋል። ተማሪዎች በእነዚህ ተግባራት እየተለማመዱ የቀረበውን የሰዋስዋዊ ትምህርት ህግጋት ቀስ በቀስ እየተረዱ ይሄዳሉ።

ከላይ ከቀረበው ገለፃ እንደምንረዳውም የመማሪያ መጽሐፍ የበለጠ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ ያለው መሆኑን ነው። ከቀረቡት መልመጃዎች ለአብነት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሆኑትን ያህል ቀጥሎ መመልከት ይቻላል።

ምሳሌ፡-

ተግባር 13

ጠቋሚ መስተዓምርን እና ስምን እንደ መሙያ የያዙ ስድስት አረፍተ ነገሮችን
መስርቱ ።

ሰባተኛ ክፍል /2007፡62/

ምሳሌ፡-

ተግባር 14

ከዚህ በታች የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች አዎንታዊና አሉታዊ በማለት ለዩ።

ሀ. የወይን ሀረግ ተሰራውን ስራ አላየችም።

ለ. ስብሰባው ላይ ብዙ ሰው አልተገኘም።

ሐ. ለቃለ መጠየቅ ያለፉ ተማሪዎች ዛሬ ይፈተናሉ።

መ. ወደ ቤታቸው የሄዱት ልጆች እንደገና መጡ።

ሠ. ራስን ከኤች.አይ.ቪ መጠበቅ ብልህነት ነው።

ረ. ጠንክሮ መስራት ለሀገር ልማት ይበጃል።

ሰ. አቶ ወርቁ ወደ አዲስ አበባ አልሄዱም።

ሰባተኛ ክፍል (2007፡95)

ከላይ ለአብነት የቀረቡት መልመጃዎች ሲቀርቡ ምንም አይነት ገለፃና ምሳሌ ሳይሰጣቸው የልመጃውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከት ዝርዝር ሁኔታውን በማጤን መልስ የሚመልሱበት የመልመጃ እጥረት ነው፡፡ ለዚህም የዚህ መልመጃ አወቃቀር ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች የእነዚህንና በሌሎች ተከታታይ መልመጃዎች በመለማመድ ወደ ትክክለኛ የሰዋስው ህግ እንዲደርሱ የሚጋብዝ የአቀራረብ ስልት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብን የተከተለ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

### 4.4.1.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

የ8ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ መርህን ተከትለው የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች ሁለት ናቸው፡፡ ይህም ከጠቅላላው የያዘው ሽፋን 6.7% ነው፡፡

በዚህ ስልት ቃላት በምሳሌ፡-

ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት መድረሻ ቅጥያዎችን ነጣጥላችሁ በመፃፍ አንብቡ፡፡

ምሳሌ፡-

ተግባር 1

**<u>ሀ</u>** **<u>ለ</u>** **<u>ሐ</u>** **<u>መ</u>**

ይታደጋል ሠንጠረዦች ምድራችን አብዛኞቹ

ይታደግ-ኣል ሰንጠረዥ-ኦች ምድር-ኣችን አብዛኞች-ኡ

| ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|
| ይሆናል | ደኖች | ዘመናችን | ዋነኞቹ |
| ይራቆታል | ስሮች | ጥናታችን | ብዙዎች |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይቀንሳል | ጥናቶች | አካላችን | አንዳንዶቹ |

ስምንተኛ ክፍል /2007፡110/

ተግባር 15

በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ጥገኛ ሀረጎችን ለይተችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. አንድ የከባቢ አየር ሙቀት መጠን ሲቀየር በሌላ የከባቢ የአየር ንብረት ሙቀት
ይተካል፡፡

ለ. የአንድ ፀባይ በአጭር ጊዜ መለስ ቀለስ ሲል የአየር ንብረት ለረጅም ዘመን
ይዘለቃል፡፡

ሐ. የአየር ንብረት ከተለወጠ በሰዎች አኗኗር ላይ ተጽዕኖ ያደርሳል ፡፡

መ. ነባር ዝርያዎች የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም ካቃታቸው በአዲስ ዝርያዎች
ይተካሉ፡፡

ሠ. የዋልታዎች ግግር በረዶ ሲቀልጥ የባህር ጠለል ከፍ ይላል፡፡

ስምንተኛ ክፍል /2007፡202/

ከላይ በአብነት የቀረበው የመጀመሪያ ምሳሌ የሰዋስው ይዘቱ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ መርህን የተከተለ ነው፡፡ ምክንያቱም ከርዕሱ እንደምንረዳው ተማሪዎች በምሳሌው መሰረት ከተሰጣቸው ሙሉ ከነመድረሻ ቅጥያ የሚገኙትን ስረወ ቃላት ቅጥያዎቻቸውን ነጣጥለው እንዲጽፉ የሚያዝ መመሪያ ቀርበዋል፡፡

ይህም ሲባል በመጀመሪያ ከነቅጥያቸው በሰንጠረዥ ውስጥ የሚገኙትን ከሀ-መ ያሉ ቃላቶች በመዘርዘር እንዲያሳዩ የሚጋብዝ መልመጃ ነው።

ለአብነት በሁለተኛ ምሳሌ ቀርቦ የሚገኘው መልመጃም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መሆኑን የመልመጃው መመሪያ በግልጽ ይጠቁማል። መመሪያውም ’’ በሚከተሉት ዐረፍተ ነገር ውስጥ ጥገኛ ሀረጎችን ለይታችሁ ፃፉ።’’ የሚለው ሲሆን በመልመጃ የቀረቡት ከሀ-ሠ የሚገኙትን ዓረፍተ ነገሮች መነሻ በመድረግ በውስጣቸው የሚገኙትን ጥገኛ ሀረጎችን ለቅመው እንዲያወጡ የሚጋብዝ የመልመጃ አይነት ነው።

በጥቅሉ ተማሪዎችም ከተሰጣቸው ገለፃ እና ምሳሌ በመነሳት እንዲሁም ከቀረበላቸው ጥቅል ነገሮች ሌላ ዝርዝር ጉዳዮችን እየተለማመዱ በሂደት የቋንቋውን ስርዓት ይካኑታል።የሆነው ሆኖ መጽሐፉ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት በብዛት አለመጠቀሙን በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል።

## 4.4.2. የመማሪያ መጽሐፍ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ ገጽታ

ይህ የአቀራረብ ስልት ምንም አይነት የሰዋስው ገለጻ ወይም ማብራሪያ አይሰጥም። ይልቁንም ተማሪዎቹ በቀረቡላቸው ምሳሌዎች አማካኝነት ቀጣይ ተግባራት በመስራት እና በመለማመድ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት/ስርዓት ለይተው እንዲያውቁ የሚያበረታታ ስልት ነው። በዚህ ጥናት ተተኳሪ መሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አብዛኞቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ ስልት ተከትለው የቀረቡ መሆናቸውን በሰነድ ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል።

### 4.4.2.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ መርህን ተከትለው ከቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች የተወሰደ አብነት ቀጥለን እናያለን።

| የክፍል ደረጃ | ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ | | |
|---|---|---|---|
| የ7ኛ ክፍል | የመልመጃ ይዘት | ገጽ | ተግባር |
| | የቃላት አውዳዊ ፍቺ | 91 | 6 |
| | በመስተአምሮች የአረፍተ ነገርንባለቤት መጠቆም | 164 | 13 |
| | አዎንታዊ እና አሉታዊ አረፍተ ነገሮች | 216 | 15 |

ምሳሌ፣

ተግባር 6

ቀጥለው ለቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት አውዳሚ ፍቺ ፃፉ::

ምሰሌ፡-ደፈረሰ----ውሀው ደፈረሰ።/ቆሻሻ/

የህዝቡ ሰላም ደፈረሰ።/ታወከ/

የጉዋደኞቹ አይን ደፈረሰ ።/ቀላ/

ሀ. እሷ ለችግሯ ቋዋሚ መፍትሔ አገኘች::

ሰውዬው የሰርጉ ቋዋሚ ነበር::

ለ. ልጁ እንቅልፉ ተነሳ::

ከዚህ በፊት የነበራቸው በሽታ ተነሳ::

ሐ. የውሃ ቡዋንቧ ብረት በሌቦች ተነቀለ::

ዛፉ ከስሩ ተነቀለ::

መ. ተማሪዎች ያቀረቡት ሀሳብ ድጋፍ አገኘ::

የቧንቧ ውሃ በመንግስት ድጋፍ ተሰራ::

7ኛ ክፍል /2007፡91/

ምሳሌ፣

ተግባር 13

የሚከተሉት መስተአምሮች የአረፍተ ነገሩን ባለቤት እንዲጠቁሙ አድርጋችሁ አስገቧቸው።

ምሳሌ፡- ያ መጽሐፍ ጠቃሚ ነው።

| |
|---|
| እነዚያ፣ እነሱ፣ ያ፣ እሱ፣ ያቺ፣ ይህ፣ እሱዋ፣ ይቺ |

ሀ. የተክሌ መማሪያ መጽሐፍ አዲስ ነው::

ለ. ልጆቹ ደስ የሚሉ አበቦች ገዙ::

ሐ. ሴትየዋ የሳድያ እናት ትመስለኛለች::

መ. አግዳሚ ወንበር ብዙ ሰዎችን ያስቀምጣል።

ሠ. ሰዎች ልብስ ከገዙ ቆይተዋል።

ረ. ልጅ እናቷን በስራ ታግዛለች ።

7ኛ ክፍል /2007:64/

ከላይ ከቀረበው አብነት የምንረዳው እስካሁን ከሌሎች መጽሐፍ በአስረጂነት ወስደን እንዳየናቸው ይህም ስለቀረበው የሰዋስው ይዘት ምንነት ማብራሪያ አልሰጠም። ይልቁንም ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምሳሌ በማስተዋል በልምምድ በቀረቡ ቃላት ላይ ያሉ ቅጥያዎችን ነጣጥለው እንዲያሳዩ ተገብዘዋል።

በልምምዱ ሂደትም ተሰመረባቸውን ቃላት አውዳዊ ፍቺ በራሳቸው እንዲገነዘቡና እንዲመለሱ የሚጋብዝ መልመጃ እንደሆነ ይታመናል። በሁለተኛው ምሳሌ መመሪያ እንደሚመለከት ተማሪዎች የቀረቡላቸውን መስተአምሮች የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት እያደረጉ እንዲጠቀሙአቸው የሚያዝ መመሪያ ነው።

ይህም እንደ መጀመሪያው ምሳሌ እንዳየነው ሁሉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ሰዋስው ይዘት አቀራረብ መርህ የተመለከተ መሆኑ ያስገነዝበናል።

### 4.4.2.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በ8ኛ ክፍል በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ይዘቶች በአብዛኛው የቀረቡት የመመሪያ መጽሐፍ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሰዋስው ይዘትን የአቀራረብ ስልትን ሰፊ ድርሻ ይዞ ተገኝቷል፡፡

ተማሪዎች የቀረበላቸውን የተለያዩ ምሳሌዎች በመመልከት የሚለማመዱባቸው በርካታ የሰዋስው ይዘቶች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥም ቀጥሎ የቀረበውን አስረጂ እናያለን፡፡

ምሳሌ፡

ተግባር 10

የሚከተሉትን ጥንድ ቃላት በምሳሌው መሰረት በማራባት ፃፉ፡፡ ምሳሌ

ሀ ለ

1. ይኖራል----------------ኖሯል

ይኖር ነበር-------------ኖሮ ነበር

2. ይፈልጋል------------ፈልጓል

ይፈልግ ነበር-------ፈልጎ ነበር

ሀ ለ

ሀ. ያገለግላል ----------------------------

ያገለግል ነበር ----------------------------

ለ. ይቀንሳል -----------------------------

ይቀንስ ነበር -----------------------------

ሐ. ይመክራል -----------------------------

ይመክር ነበር -----------------------------

ስምንተኛ ክፍል /2007: 183-184/

ምሳሌ፡

ተግባር 7

ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት በተመሳሳይ እና በተቃራኒ ፍቻቸው አርፍተ ነገር መስርቱ።

ምሳሌ፡- ደልደል ያለ--------------ወፈር ያለ---------ተመሳሳይ ፍቺ

ወ/ሮ አየለች ወፈር ባለ ሰውነታቸው የአገር ልብስ ለብሰዋል።

ደልደል ያለ--------------ከሳ ያለ------------ተቃራኒ ፍቺ።

ወ/ሮ አለምነሽ ከሳ ባለ ሰውነታቸው ላይ የለበሱት ቀሚስ ያሚራል።

ሀ. ማገዝ መ. ተበጥሯል

ለ. ቁልል ሠ. አጣደፈኝ

ሐ. ተሸፈነ ረ. እንዳቀረቀሩ

8ኛ ክፍል /2007፡224/

ይህም የመመሪያ መጽሐፍ ከዚህ ቀደም እንዳየናቸው መጽሐፉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ መርህን የተከተለ መሆኑን ከቀረበው አብነት እንገነዘባለን።

በአጠቃላይ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሰዋስው ይዘት የአቀራረብ መርህ በተመለከተ ታላሚ መጽሐፍ ጠንካራ ጎን ያላቸው መሆኑ በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል።

## 4.4.3. የመማሪያ ሁለቱን የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ በስብጥር የመጠቀም ገጽታ

በአንድ የቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ዘንድ በአንድ አይነት የአቀራረብ ስልት ብቻ መቅረር የለባቸውም:: ምክንያቱም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ወይም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ የእራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን ያላቸው መሆኑን በምእራፍ ሁለት ተመልክተናል።

አንዳንድ ተማሪዎች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ለአቀባበላቸው ሲመቻቸው ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሰዋስው ይዘት የአቀራረብ ስልት ሊመቻቸው

ይችላል:: ምክንያቱም አንዳንዴ በትምህርትነት የሚቀርቡ የሰዋስው ይዘቶች በተመሳሳይ የአቀራረብ ስልት ሲቀርቡ አሰልቺ ይሆናሉና ።

ይህም በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። የትምህርት ይዘቶች መክበድ እና መቅለልም በራሳቸው የአቀራረብ ስልት ሊያስመርጡ ይችላሉ። አንዳንዶቹ ጥልቅ ማብራሪያ እና ምሳሌ ካልተሰጣቸው የማይሞክሩ ሲሆኑ ሌሎች ግን በቀላሉ ሊሰሩ ይችላሉ። ስለዚህ ላይ የተገለፁትን ችግሮች ሊያቃልል የሚችለው ሁለቱን የሰዋስው ይዘቶች ያጣመሩ የአቀራረብ ስልቶች በፈረቃ ወይም በስብጥር መጠቀም ነው። ከዚህ በመቀጠል የታላሚ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘት የስብጥር አጠቃቀም ሂደትን እንቃኛለን።

#### 4.4.3.1. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

ሠንጠረዥ 11. የመማሪያ መጽሐፍ ሁለቱን የሰዋስው ይዘቶች በስብጥር የመጠቀም ገፅታ

| የክፍል ደረጃ | ከአጠቃላይወደ ዝርዝር የተደራጁ የሰዋስው ይዘቶች ብዛት | | ከዝርዝርወደ አጠቃላይ የተደራጁ የሰዋስው ይዘቶች ብዛት | | ጠቅላላ የሰዋስው ይዘት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | 30 |
| 7ኛ | 2 | 6.7 | 28 | 93.3 | |

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ በውስጡ ከያዛቸው 30 /ሰላሳ/ የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ 2/ሁለት/ የሰዋስው ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልትን ተከትለው ሲቀርቡ በመቶኛ ሲሰላም 6.7% ብቻ መሆኑን የሰነድ ፍተሻው ያሳያል ። ሌሎች መልመጃዎች ግን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ ስልትን ተከትለው ቀርበዋል።

የነዚህም መልመጃዎች በታላሚው መጽሐፍ ውስጥ ያላቸው ሽፋን በመቶኛ ሲሰላ 93.3% መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

በአጠቃላይ የ7ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ሁለቱን የሰዋስው ይዘቶች የአቀራረብ ስልት አመጣጥኖ ከመጠቀም አኳያ ችግር ያለባቸው ሆነው ታይቷል።

#### 4.4.3.2. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

ሠንጠረዥ 12. የመማሪያ መጽሐፍ ሁለቱን የሰዋስው ይዘቶች በስብጥር የመጠቀም ገፅታ

| የክፍል ደረጃ | ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የተደራጁ የሰዋስው ይዘቶች ብዛት | | ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የተደራጁ የሰዋስው ይዘቶች ብዛት | | ጠቅላላ የሰዋስው ይዘት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | 30 |
| 8ኛ | 13 | 43.3 | 17 | 56.7 | |

የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ በውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ 13ቱ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ስልትን ተከትለው የቀረቡ ሲሆን በመፃፍቱ ውስጥ ያላቸው ሽፋን በመቶኛ ተሰልቶ 43.3% ሆነዋል። ይህ መሆኑ ደግሞ ሁለቱን የመልመጃ አቀራረቦች አሰባጥሮ መያዙን ይጠቁመናል።

ሌላው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ስልትን የተከተሉ መልመጃዎች ናቸው። የነዚህ መልመጃዎች አጠቃላይ የመቶኛ ሽፋን ደግሞ 56.3% መሆኑን የሰነድ ፍተሻው ጥናት አሳይቷዋል።

በአጠቃላይ ሁለቱን የሰዋስው ይዘቶች የአቀራረብ ስልት አመጣጥኖ ከመጠቀም አኳያ የስምንተኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ከሰባተኛ ክፍል የተማሪው መጽሀፍ በተሻለ ሁኔታ የአቀራረብ ስልት በመጠቀም አመጣጥኖ መቅረቡን መመልከት ተችሏዋል።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና አስተያየት

## 5.1.ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የተስማማ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል ላይ የተጠና ጥናት ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋነኛ የትኩረት በ2007 የተዘጋጁ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ይዘት አመራረጥ እና አደረጃጀት መገምገም የጥናቱ አብይ ስራ ነው፡፡

ይህን የጥናቱን አብይ ትኩረት መነሻ በማድረግ በታላሚዎቹ የክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙት መጽሐፍ በጥልቀት በመፈተሽ የታላሚዎቹን መጽሐፍት የሰዋስው ይዘቶች አመራረጣቸውን እና አደረጃጀታቸው በምን መልኩ እንደ ተደራጁ እንዲሁም መጽሐፉ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን መፈተሽ የዚህ ጥናት ዋነኛው መዳረሻ ነው፡፡

አጥኝው ጥናቱን ዳር ለማድረስ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መርሆች ከመጻህፍት ፣ ከጥናታዊ መፅሔቶች እና ከቀደምት ጥናቶች ውስጥ የተለያዩ ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተዛማጅነት ያላቸውን ጽሁፎች በመሰብሰብ በምዕራፍ ሁለት ላይ አጠናቅሮ አቅርቡዋል፡፡

ምሁራኑ በሰጡት አስተያየት መሰረት የአንድ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለመገምገም የሚያስችሉ መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል፡፡ በእነዚህ የመገምገሚያ መስፈርቶች መሰረት የጥናቱ ታላሚ የሆኑትን ሁለት የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ማለትም የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ እንደየክፍል ደረጃቸው ከተለያዩ የቋንቋ መጽሐፍ ማዘጋጅያ መርሆች አኩዋያ በቅደም ተከተል ተፈትሸዋል፡፡

የጥናቱ ታላሚ የሆኑትን መጽሐፍ ሁለቱንም በመውሰድ በአንድ የመገምገሚያ መስፈርት መሰረት በመፈተሽ ትንተናው ተካሂዷል፡፡

ተለጣጣቂነትን ከዝቅተኛ ክፍል ወደ ከፍተኛ ክፍል ተለይተው ሲፈተሽ በተያያዥነትም በመጀመሪያዎቹ በግምገማው ሂደት ላይ የታዩ ድክመቶች እና ጥንካሬያቸውን ለመለየት ጥረት ተደርጓል፡፡

ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ ያስችል ዘንድም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በስነ-ድምፅ፣ በስነ-ምዕላድ፣ በስነ-አገባብ፣ እና በስነ-ፍች በሚሉ ንዑሳን ክፍሎች ተለይተዋል፡፡

በእነዚህ የሰዋስው ክፍሎች ስር ተዘርዝረው የቀረቡ ይዘቶችም በመገምገሚያ መስፈርቶች አማካኝነት ተዳስሰዋል፡፡ እንዲሁም በመጨረሻም በዚህ መልኩ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በአይነታዊና በመጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡

በታላሚ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች በአብዛኛው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ ስልትን የተከተሉ ናቸው፡፡ ያም ሆኖ ግን ጥቂት የሰዋስው ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ቀርበዋል፡፡

ይህም የሚያሳየው በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራብ ስልት እጥረት ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ ተለጣጣቂነትን በተመለከተ ተተኳሪ የመማሪያ መጽሐፍ ጉድለት ታይቶባቸዋል፡፡ በጊዜ ሂደትም የታየባቸው ለውጥ የለም፡፡

## 5.2. አስተያየት

በጥናቱ ታላሚ የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ እና አደረጃጀት ፍተሻ ላይ የታዩ ድክመቶች ማስተካከያ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት የመፍትሔ ሃሳቦች በጥናቱ አቅራቢ ቀርበዋል፡፡

- በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀት እና አቀራረብ መሰረታዊ መርሆችን መሰረት ቢያደርጉ እና ፍትሃዊ ስርጭት ቢኖራቸው፤
- በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚካተቱ የሰዋስው ይዘቶች ከምዕራፍ፣ ከክፍል ክፍል ስፋት እና ጥልቀት እየጨመሩ እንዲሄዱ ቢደረግ፤
- የመማሪያ መጽሐፍ የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ልምድ ያላቸው ቢሆኑ ወይም ግንዛቤያቸውን ሊያጎለብት የሚችል ስልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ ቢመቻች፤
- ከዚህም ባሻገር በተለይ የተከታታይነትን እና የተለጣጣቂነትን ችግር ለመፍታት ከፍተኛው የክፍል ደረጃ በዝቅተኛው የክፍል ደረጃ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ላይ የሚመሰረት ቢሆን፤
- የመማሪያ መጽሐፍ በአገባቡ ታስቦባቸው በበቂ የጊዜ ሂደት ቢዘጋጁ ፤
- ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ፣ተማሪዎች እና መምህራን በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች አመራረጥን እና አደረጃጀትን እንዲገመግሙ ሁኔታዎች ቢመቻቹ፤
- ምጋቤ መልሶችም ተፈትሸው ተግባራዊ ቢደረጉ ፤
- የመማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጁበት አላማ በመግቢያው ላይ ቢገለፅ እና
- የመማሪያ መጽሐፍ ቅርፃቸውም ለተማሪዎች አያያዝ የሚመቹ ቢሆኑ የሚሉ የመፍትሄ ሀሳቦች ሰጥቻለው።

## ዋቢ ፅሁፎች


ሐዋዝ ወልደየስ። (2000)። «በአዲስ አበባ ከተማ በአማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የስዋስው ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ንፅፅራ ጥናት ።» የሁለተኛዲግሪ ጥናታዊ ፅሁፍ ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ማረው ዓለሙ።(1998)። የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ስነ ዘዴ ።አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት

ባዩ ተሾመ ። (2004)።‹‹በደቡብ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ 2ኛው እርከን አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ እና አደጃጀት ግምገማ›› የ2ኛው ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ተስፋዬ ሸዋዬ። (1981) ‹‹ ስነ-ልሳን እና ቋንቋ ማስተማር›› አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ ክፍል (ያልታተመ

እምሻው ማሞ። (2005)። ‹‹ለዘጠነኛ እና ለአስረኛ ክፍል በተዘጋጁት ከ1968-2004ዓ.ም የአማርኛ ቋንቋ እና መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ›› የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

እስሌማን አባይ። (2003)።‹‹ በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻህፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስው አንፃር›› የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ኪዳነወልድ ክፍሌ። (1948)። መጽሀፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት ሃዲስ።አዲስ አበባ፤አርክቲክ ማተሚያ ቤት

ያለው እንዳወቀ። (1998)። የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር። አልፋ አሳታሚዎች።

ዮሐንስ አረጋዊ ። (2003)።‹‹ በትግራይ ክልል ለ9ኛና ለ10ኛ ክፍል በተዘጋጁት የትግርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ትምህርቶችን አመራረጥ አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ›› የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ ።አዲስ አበባ ዩኒቨሲቲ።

ጌታሁን አማረ። (1989) ። ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ። አዲስአበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት

ደስታ ተክለወልድ። (1992)። አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርክቲክ ማተሚያ ቤት

Atkins, Jetal (1995). Skills Development Methodology. (part-1) Addis Ababa: AAU Printing Press.

Batston,R. (1994). Language Teaching Grammar. oxford OUP.

Brown, H.D. (2000). Principle of Language Learning and Teaching (4th ed). New York: Addison- Wesley Longman,Inc.

Cunnigs worth, A. (1995). Choosing Your Course Book. Oxford Heineman Publisher.

Crystal, D. (2004). Rediscover Grammar.Second edition;London;Longman.

Ellis, R. (2007). Second Language Acqustion.Oxford: Oxford Universty Press.

Felder,R,& Henriques ,E. (1995). Learnig and Teaching Styes in Foreign and Second Language Education.Foreign Language annals 28(1),21-31.

Harmer,J. (1987). Teaching and Learnig Grammar. London : Longman

Hopkins, David. (2002). A Teacher's Guide to Class room Research. (3rd .ed.). Great Bretain: Open University press

Leech, G. (1994). Students Grammar -Teachers Grammar -Learnes Grammar : Grammar and the Language Teacher. PP.17-30 Hemel Hemp stea printice-Hall.

Nunan, D. (1988). Syllabus Design. Oxford: Oxford University Press.

Patel and Jain. (2008). English Language Teaching: Methods,Tools &Techiques. Sunrise publishers & Distribution: Jaipur.

Rutherford, W.E. (1987). Second Language Grammar. Learnig and Teaching. London Longman

Sheldon,L.E. (1988). ''Evaluation ELT Text Book and Materials. ELT Journal.Vol 42.No. 4,237-246

Simensen, Aud Marit (1998). Teaching of forgeign language .Olso Fragbokforlaget.

Stern,H.H. (1992). Issues and Options in Language Teaching. Oxfored:Oxford University press.

Tonkyn,A. (1994). <<Introduction Grammar and the Language Teacher.>> in Bygate M.etal. (eds) Grammar and the Language Teachers (pp.1-14) New York: prentice Hall

Tudor, lan. (1996). Learner Centerdness as Language Education. Cambridge, CUP

Tyler, R.W. (1949). Basic Principles of Curriculum and Instruction. Chicago:CUP

Widodo ,H. (2006). Approaches and Procedures for teaching grammar. English teaching: practice and critique. Vol.5, No.1,pp.122-141

Yashpal and Sunil, (2005). Teaching of English A book Witten for students of B.Ed and DIET and Coverting the Syllabus of Major Indian Universities. Jadamba Publishing Company. New Delhi.